NOTE

# The Development of Modern Criminal Justice Processes and Institutions in Ethiopia (1907-1974): An Overview

Simeneh Kiros Assefa ♣

## Abstract

This note briefly discusses the institutional and process developments in Ethopia's modern criminal justice. There is a close relationship between political administration and justice administration considering the issue of judicial independence in a historical context. The year 1907 is taken as a starting point in the development of criminal norms and institutions because the Ministry of Justice was established and Afe Negus Nesibu was appointed Minster of Justice. The institutional and normative developments in this period were merely reactive to problems. Twelve judges were appointed to help the Minster of Justice who was entrusted to see all the cases by himself. Procedural rules were introduced as schedules in order to manage the inflow of cases. The enactment of the 1930 Penal Code helped judges determine sentences rather than sending convicts to the governor for sentencing. Regulation of appeal and preliminary processes such as providing a copy of judgement were introduced. The second phase in Ethiopia's modern criminal justice system started from 1941 onward because this year is a landmark for the establishment of modern legislation and modern criminal justice institutions. The police were established as an investigation institution that executes orders given by the court. Prison was established signaling imprisonment as a mode of punishment. The prosecution institution was established under the Ministry of Justice. Thereafter, several substantive and procedural rules have been adopted governing the initiation of cases, summons, evidence, judgement and appeal. The last institution established during this period was the judicial organ.

## Keywords

criminal justice, criminal justice process, criminal justice institutions, Ethiopia

**DOI** http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v18i1.8

**Suggested citation**:

Simeneh Kiros Assefa (2024). "The Development of Modern Criminal Justice Processes and Institutions in Ethiopia (1907-1974): An Overview" (Amharic), 18(1) *Mizan Law Review*: 215-240.

---

♣ Simeneh Kiros Assefa (PhD), Associate Professor of Law, Addis Ababa University School of Law.
E-mail: simeneh@simenehlaw.com
ORCID: https://orcid.org/0000-0003-0915-9360

# ዘመናዊ የወንጀል ፍርድ ሥራ አካሄድ እና የተቋማት እድገት አጭር ዳሰሳ

ስሜነህ ኪሮስ አሰፋ♣

## አፅህሮተ ጽሑፍ

ይህ ጽሑፍ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓታችን በዘመናዊ መልክ ተደራጅቶ አሁን የደረሰበት ደረጃ ከመድረሱ በፊት የሄደበትን የእድገት ደረጃ በአጭሩ ይዳስሳል። እንደመነሻ የተወሰደው ፲፱፻ ዓ/ም ሲሆን ይህም የመጀመሪያው የፍትሕ ሚኒስቴር ተቋቁሞ አፈ-ንጉሡ የመጀመሪያው የፍትሕ ሚኒስትር የሆኑበት፣ እንዲሁም አሥራ ሁለት ዳኞች የተሾሙበት ዘመን ነው። በዚህ ዘመን የመንግሥት አስተዳደርና የዳኝነት ተግባር የተለያዩ አልነበሩም። በመሆኑም የመጀመሪያው ዳሰሳ ከ፲፱፻ እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ያለውን የለውጥ ሂደት የሚሸፍን ሲሆን በዋናነት የተቋማቱን ምሥረታ የሚመለከት ነው። አነስተኛም ቢሆኑ አሠራራቸውን የሚገዙ ድንጋጌዎች በእነዚህ ዓመታት ተደንግገዋል። ሁለተኛው ዳሰሳ ከኢጣሊያ ወረራ ፍፃሜ በኋላ ከ፲፱፻፴፬ ዓ/ም ጀምሮ እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ያለውን ወቅት ይሸፍናል። በዚህ ወቅት ነጋሪት ጋዜጣ እንደ ኦፊሴል የሕግ ጋዜጣ ሆኖ ከቆመ በኋላ ዘመናዊ አስተዳደር ተመሠረተ፤ ስለሕግ አወጣጥ ሕግ ወጣ፤ ብዙ ፍሬ ሕግጋት ታወጁ፤ የሥነ-ሥርዓት ሕግጋትም ጸደቁ። የዳኝነት አስተዳደርን የሚያሳልጡ የተለያዩ የፍትሕ ተቋማት በዘመናዊ መልክ ተደራጅተው ሥልጣናቸው ተደነገገ። የወንጀል ምርምራ፣ የዳኝነት ሥልጣን፣ ክስና መልስ፣ የይግባኝ ሥርዓት፣ ስለልዩ ልዩ ችሎቶች መኖር የሚገዙ ደንቦች ተደነገጉ። በመጨረሻም የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ተመሠረተ። በዚህ ዘመን የዳኝነትና የፍትሕ ተቋማት ምሥረታ የተጠናቀቀ ይመስላል።

**ቁልፍ ቃላት**

የወንጀል ፍትሕ፣ የወንጀል ፍትሕ ሂደት፣ የወንጀል ፍትሕ ተቋማት፣ ኢትዮጵያ

**የጥቅስ አጠቃቀም**

ስሜነህ ኪሮስ አሰፋ (2016 ዓ.ም)፣ “ዘመናዊ የወንጀል ፍርድ ሥራ አካሄድ እና የተቋማት እድገት አጭር ዳሰሳ”፣ *ሚዛን የሕግ መጽሔት*፣ ቅጽ 18፣ ቁ. 1፣ ገጽ 215-240

## ይዘት

፩ መግቢያ

፪ የመጀመሪያው እርከን የለውጥ ጥረቶች፣ ከ፲፱፻ እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ/ም

፫ የሁለተኛው እርከን መሠረታዊ ለውጥ፣ ከ፲፱፻፴፬ እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም

፬ ስለሕግ አረዳዳችን አንዳንድ ምልከታዎች

፭ ማጠቃለያ

---

♣ ስሜነህ ኪሮስ አሰፋ (ፒኤችዲ)፣ ተባባሪ ፕሮፌሰር፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሕግ ት/ቤት
ኢሜይል: simeneh@simenehlaw.com
ORCID: https://orcid.org/0000-0003-0915-9360

## ፩ መግቢያ

ስለፍትሕ ሲወሳ ባለሙያ ላልሆነው ሰው ቀድሞ የሚታሰበው የወንጀል ዳኝነት፣ በተለይም፣ እስራትና የሞት ቅጣት ነው ። ይህም የመንግሥት ሥልጣን መገለጫ ተደርጎ የሚታይ ከመሆኑም በላይ በቀደመው ዘመን ፍርድ ሲሰጥ ብዙኃኑ ስለፍርዱ ፍትሐዊነት ጥርጣሬ አልነበረውም። እንዲያውም በከባድ ወንጀል ጉዳይ የፍትሕ ሂደቱ የክስ መስማትና ምርመራ አንድ ላይ በአደባባይ በንጉሡ ይከናወን በነበረ ጊዜ ለንጉሡ መለኮታዊ መገለጥ እንደተጨመረላቸው ይታሰብም ነበር።[1] ከአፄ ሥርዓት ባህሪያት መካከል አንዱ እነዚህ የዙፋን ችሎት ፍርዶች ናቸው።[2]

የዳኝነትና የአስተዳደር ሥራ የማይለያዩ ስለነበሩ ዳኝነት ይሰጥ የነበረው በንጉሠ ነገሥቱ እና በእርሱ ሹመኛ አስተዳዳሪዎች ነበር። አስተዳደርና ዳኝነት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። በመሆኑም የቀደመው ዘመን የኢትዮጵያ አስተዳደር በአስተዳደርና በዳኝነት ሥራ መካከል ልዩነት አልነበረውም። ንጉሠ ነገሥቱ በዙፋናቸው ዳኝነት እንደሚቀመጡ ሁሉ አገረ-ገዥው በሚገዛው ግዛት የሚነሱ የዳኝነት ጥያቄዎችን እየተመለከተ ዳኝነት ይሰጥ ነበር። በሞት ከሚያስቀጡ ወንጀሎች በቀር በሁሉም ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ነበራቸው። ዳኝነት አለመስጠት ከፍተኛ ጥፋት ስለነበር፣ ንጉሠ ነገሥቱ ለየአገሮቹ ገዥዎች ሕዝቡን ዳኝነት እንዳይነፍጉት ይነግሩ ነበር።

ከዚህም ባለፈ በተለያዩ ምክንያቶች የአገሩ ገዥ በንጉሠ ነገሥቱ ከሥልጣኑ ቢነሳና ገዥ ባይመደብለት፣ ንጉሡ ለአገሩ ወንበር (ዳኛ) ይሾሙለታል።[3] ይህም ማለት ገዥው ሁሌም በዳኝነት ያገለግላል ወይም ዋናው ዳኛ ሁሌም አገረ ገዥው ነው ማለት ሳይሆን፣ አገረ ገዥው ዳኛ የመሆን እድሉ እጅግ ከፍ ያለ ነበር። በተለይ በ፲፱፻፴፬ ዓ/ም የኢትዮጵያ ግዛት በ፲፪ አውራጃዎች ሲከፋፈል፣ የአውራጃው፣ የወረዳው ገዥ እና ምስለኔው በዳኝነት እንደሚያገለግሉ የተደነገገ ሲሆን፣ ዳኝነት ብቸኛ ተግባር የተደረገው ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ብቻ ነበር። አስተዳዳሪዎች ከዳኝነት ሥራ የተላቀቁት ቆይተው በ፲፱፻፶፭ ዓ/ም አካባቢ በተለይም የዳኞች አስተዳደር አዋጅ ከወጣ በኋላ ነው።

ይህ አጭር ጽሑፍ የኢትዮጵያ ዘመናዊ የወንጀል ፍርድ ሂደት እድገትን ይዳስሳል። ለዚህም እንደመነሻ ተደርጎ የተወሰደው ፲፱፻ ዓ/ም ነው። ምክንያቱም መንግሥት በዚህ ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ የመንግሥት የዳኝነት አካል ራሱን ችሎ ያቋቋመ ሲሆን ከዚህ ጊዜ በኋላ የታዩት ለውጦች ተቋሙ አሁን የያዘውን ቅርጽ ለመያዙ መሠረታዊ

[1] *ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በመጀመሪያው የንግሥና ዘመናቸው ሕዝብን ያስደመሙ ሦስት ፍርዶች ሰጥተዋል። የመጀመሪያው ፍርድ በወልደ አማኑኤል እና በተስፋ ሚካኤል መካከል በነበረው ክርክር ነው፤ ሁለተኛው በአለቃ ኪዳነ ወልድ ላይ የቀረበውን ክስ የሚመለከት ሲሆን ሦስተኛው የይፋቱ የርስት ባላደራው ልጅ ግድያ ወንጀልን የተመለከተ ነው። ፍርዱን የሰሙ ሁሉ ለንጉሡ መለኮታዊ መገለጥ (ሥልጣን) እንደተሰጣቸው ተቆጠረ። ይህም ማለት ንግሥናቸው የተገባ ነው እንደማለት ነበር።* Gebre-Sillasie, *Chronicles of the Reign of Menilek II King of Kings of Ethiopia,* Vol I (Trans. Dominique Lusser, Tsehai Publisher 2017) 133-45.

[2] አበራ ጀምበሬ፣ *የኢትዮጵያ ሕግና የፍትሕ አፈጻጸም ታሪክ ከ1426 እስከ 1966 ዓ/ም* (ሻማ ቡክስ 2006 ዓ/ም) ገጽ 145-59።

[3] የጎጃሙ ገዥ ራስ በዛብህ በ1897 ዓ/ም በወንጀል ተከሰው ዳግማዊ ምኒልክ እስራት ፈርደውባቸው ወደ አፍቀራ ሲላኩ አገሩ ገዥ ባይኖረውም ዳኝነት እንዳይጓደል በማለት ይፋቴው ግራ/ች ወልደዮሐንስ ወንበርነት (ዳኝነት) ተሹመው ለደጃች ሥዩም አስረክበው እስኪመጡ ድረስ ሲያገለግሉ ቆይተዋል። መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፤ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት 1896-1922* (ሦስተኛ እትም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ፪ሺ. ፪ ዓ/ም) ገጽ 27-29።

በመሆናቸው ነው። ጎላ ብለው ሊጠቀሱ የሚችሉት በኢትዮጵያ ዐውድ የሕግ ሥርዓቱ ከሃይማኖታዊ ሕግጋት ወደ ንጉሣዊ ሕግጋት መሸጋገሩን፣ የዳኝነት ተቋማቱም ወደ መንግሥት-መር የዳኝነት ተቋማት መሸጋገራቸውን፣ በተለያየ ዘይቤ ለምሳሌ በተጠየቅ ሥርዓት[4] ይደረግ የነበረው የክርክር አመራር በመንግሥት በወጣ ሕግ መሠረት በተዘረጋ የክርክር ሥነ-ሥርዓት መመራት መጀመሩን፣ እንዲሁም የንጉሡ የዳኝነት ሥልጣን ለሁሉም የአገሪቱ ግዛቶች ለዜጎች ተደራሽ ለማድረግ መሠረታዊ ሥራዎች መሠራታቸውን ነው።

ይህ ጥናት የሚመለከተው ከ፲፱፻ ዓ/ም ጀምሮ እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ያለውን ጊዜ ሲሆን ይህም ጊዜ በሁለት የሚከፈል ነው። የመጀመሪያው ጊዜ ከ፲፱፻ እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ያለውን ይሸፍናል፤ በዋናነት የተቋማቱን ምሥረታ የሚመለከተውና አሠራራቸውን የሚገዛው ሕግ በጥቂቱ ተደንጓል። ሁለተኛው ክፍል ከኢጣሊያ ወረራ ማብቂያ በኋላ ከ፲፱፻፴፬ ዓ/ም ጀምሮ ያለውን ይሸፍናል። ይህ ወቅት በእንግሊዝ መንግሥት የቴክኒክ ድጋፍ ነጋሪት ጋዜጣ እንደ ኦፊሴል የሕግ ጋዜጣ ሆኖ ከቆመ በኋላ፣ ዘመናዊ አስተዳደር የተመሠረተበት፣ ስለሕግ አወጣጥ ሕግ የወጣበት፣ ብዙ ፍሬ ሕግጋት የታወጁበት፣ የሥነ-ሥርዓት ሕግም የወጣበት ጊዜ ነበር። የዳኝነት አስተዳደርን መሠረት ያደረጉ የተለያዩ ሕግጋትም ወጥተዋል። በዚህ ዘመን የዳኝነትና የፍትሕ ተቋማት ምሥረታ ተከናውኗል።

አንድ የፍርድ ሂደት «ሥርዓት» ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለው በፍርድ ሂደቱ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት ተቋማት፣ ተቋማቱ የሚሠሩባቸው ሕግጋት፣ እንዲሁም የተቋማቱ የአሠራር ዘይቤ እና እነዚህ ሦስቱ ያላቸው መስተጋብር ተደንግጎ ሲተገበር ነው። እነዚህ የፍርድ ሂደት ዋልታዎች ከ፲፱፻ ዓ/ም ጀምሮ ቀስ በቀስ እየተተከሉና እየጎለበቱ ስለሄዱ በአፈጣጠራቸውና በአስተዳደጋቸው ላይ አጠር ያለ ሐተታ ያስፈልጋል።

ለዚህ ጥናት ምንጭ የሆኑት በየጊዜው የወጡት ሕግጋትና ደንቦች፣ በተለያየ ጊዜ የተሰጡ ውሳኔዎች፣ በጉዳዩ ላይ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች በተለያየ አጋጣሚ ስለሚያውቁት ነገር የጻፏቸው ጽሑፎች ናቸው። በዚህ ዘመን ያሉትን የተወሰኑ ሥራዎችና ሰነዶች ስንጠቅስ ያልተጠቀሱትን ታሳቢ በማድረግ ነው። ለምሳሌ ፍትሐ ነገሥት ስለዳኛ አሿሿም፣ ስለምስክር አሰማም፣ ስለፍርድ አሰጣጥ፣ እና ስለዳኞች ሥነ-ምግባር ይደነግጋል። ስለዚህ ይህ ጥናት ከ፲፱፻ ዓ/ም ሲጀምር፣ ከዚያ በፊት የነበረውን በብዙ መቶ ዓመታት የዳበረ የዳኝነት ሙያና ሥነ-ምግባር ታሳቢ በማድረግ ነው።

የፍርድ ቤቶችን ታሪክና እድገት የሚመረምሩ ጸሐፍት ስለተቋሙ አመሠራረት፣ ስላለው ሥልጣን፣ በምን ደረጃ እንዲሠራ እንደታሰበ፣ በሂደት ይህ ሥልጣን እንዴት እየዳበረ እንደመጣ ይመረምራሉ። በዚሁ መሠረት ፍርድ ቤቱ እንደ መንግሥት ሦስተኛ አካል ሆኖ ሌሎቹን ሁለቱን የመንግሥት አካላት ተጠያቂ በሚያደርግ መልኩ ስለመሥራቱ፣ ሥልጣኑ እንዴት እንደዳበረ ወይም እንዳልዳበረ፣ በተቋማቱ መካከል ስለላው መስተጋብርና መሰል ጉዳዮች ይመረምራሉ፤ በሂደትም ፍርድ ቤት እንዴት ለፖለቲካው ሥርዓት መሣሪያ እንደነበር ወዘተ. የሚመረምሩ ናቸው።

የፍርድ ቤትን የሥራ ክንውን የሚተነትኑ ጸሐፍት በዋናነት የሚመረምሩት ፍርድ ቤቱ የሚሠራበትን ሕግ በምን ዓይነት መልኩ እንደሚረዳውና እንደሚተገብረው ነው።

[4] አበራ ጀምበሬ «ተጠየቅ ሙግት፥ ልማዳዊው የኢትዮጵያ የክርክር ስልት» *የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት*፣ ቅጽ ፲፫ (፲፱፻፸፬ ዓ/ም)። የተጠየቅ ሙግት ሥርዓት በአብዛኛው ስለተለመደ ነው እንጅ የክርክር ሥርዓት በፍትሐ ነገሥቱ ተደንግጎ ማገልገሉ እሙን ነው።

ይህም ዳኞች የሚከተሉትን የሕግ አረዳድ፣ ጭብጥና ፍሬ ነገርን ከሕጉ ጋር የማዛመድ ብቃት እንዲሁም ስለሕጉ ንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፍ ያላቸውን ግንዛቤ የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚገለጠው በዳኞቹ ተግባርና በፍርድ ቤቱ አሠራር ነው፡፡ ስለዚህ ፍርድ ቤቱ የሚሠራበት የሕግ ምርምር ከፍርድ ቤቱ አሠራር ስልትና ዘዴ ጋር ተዳብሎ የሚመረመር ነው፡፡

ይህ ጥናት በዋናነት የሚመለከተው የፍርድ ቤቱንና ሌሎች የፍትሕ ተቋማት መቋቋምና የሥልጣናቸውን ሁኔታ ነው፡፡ የፍርድ ቤቶችን ዝርዝር አሠራር የሚመለከቱና መሰል ጉዳዮች ከፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት ለውጦች አኳያ የፍርድ ቤቶችንና ሌሎች የወንጀል ፍትሕ ተቋማት ደጋጋሚ መፍረስ፣ መደራጀት፣ አወቃቀርና ምደባ ያስከተሉ በመሆኑ በዚህ አጭር ጽሑፍ ማጠቃለል አይቻልም፡፡

የመንግሥት አደረጃጀትና አሠራር በምዕራቡ ዓለም የመንግሥት ሥልጣን በሦስት አካላት እንደሚከፋፈለው ሳይሆን የአስተዳደርና የዳኝነት ተግባራት አዘውትረው ተዳብለው ይከናወኑ እንደነበር ከላይ በመግቢያው ሁለተኛና ሦስተኛ ፓራግራፎች ተመልክተናል፡፡ የሚቀጥለው የጽሑፉ ክፍል ስለመጀመሪያው የፍርድ ቤቶች አመሠራረት ሂደት የሚገልጽ ሲሆን የጽሑፉ ሦስተኛ ክፍል ከኢጣሊያ ወረራ ማብቂያ በኋላ ያለውን የፍርድ ሂደት ያስረዳል፡፡ ከ፲፱፻፴፬ ዓ/ም ጀምሮ እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በነበሩት ሦስት አሠርታት ከፍርድ ቤቶች በተጨማሪ ሌሎች የፍትሕ ተቋማትን ለመመሥረትና ተቋማቱ የሚሠሩበትን ደንብና ሕግ ለማውጣት መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እንደነበር የወቅቱ ክንውኖች ያሳያሉ፡፡ ይህ ጥናት ኋላ ብለው የሚታዩትን ክስተቶች የሚዳስስ ነው፡፡

## ፪ የመጀመሪያው እርከን የለውጥ ጥረቶች - ከ፲፱፻ እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ/ም

በየትኛውም የፍትሕ ሥርዓት በሚደረጉ ጥናቶችና ምርምሮች ፍርድ ቤቶች ከመንግሥት አስተዳደር ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት፣ የፍትሕ ተቋማት ምሥረታ፣ ሥልጣን፣ የአሠራር ማሻሻያ ጥረቶችና ክንውኖች ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡ ፍትሕ ሕዝባዊ አገልግሎት እንደመሆኑ የፍትሕ ሥርዓት በእውነት፣ በፍትሕና በሕዝብ አመኔታ ላይ የተመሠረተ መሆኑ የብቃት ደረጃውን ያሳያል፡፡ የፍትሕ ሥርዓትም ይህንኑ ተፈጥሯዊ ሂደት ተከትሎ የሚጀምር፣ የሚያድግና፣ የሚጎለብትና የሚሰክን እንደመሆኑ ሂደቱን መፈተሽ አስፈላጊ ነው፡፡

የወንጀል ፍትሕ ሂደትን በተመለከተ የትኛው ሥርዓት መቼ እንደተተከለ የሚያሳይ ሰነድ ማግኘት አዳጋች ቢሆንም፣ ብዙ ሥርዓቶች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ የስርቆት ወንጀልን በተመለከተ ሌባሻይ የምርመራ ዘዴ ሲሆን፣[5] በግድያ ወንጀልና በከብት ዝርፊያ ደግሞ ሹማምንቱና የአካባቢው ነዋሪዎች አፈርሳታ ወይም አውጫጭኝ የሚባል ባህላዊ የምርመራ ዘዴዎች በኢትዮጵያ ሲተገበሩ ቆይተዋል፡፡ እነዚህ ሥርዓቶች በተለያዩ ሰዎች ስለሚተገበሩ በማን እንደሚተዳደሩ ብዙ ግልጽ አይደለም፡፡[6]

---

[5] የሌባ ሻይ ወንጀል ምርመራ ውጤታማ እንዳልነበረ ሞክረው ማረጋገጣቸውን ራስ እምሩ አስፍረዋል፡፡ እምሩ ኃይለ ሥላሴ፣ *ካየሁት ከማስታውሰው፣* 2ኛ እትም (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፪ ሺ ፪ ዓ/ም) ገጽ 123-25፡፡

[6] የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ በልጅ ኢያሱ ዘመን ሦስት መሠረታዊ መሻሻሎች ተደርገዋል፡፡ የመጀመሪያው ቁራኛን ማስቀረት ነው፤ ሁለተኛው የሌባሻይ ምርመራን መገደብ ሲሆን ሦስተኛው የመንግሥት ሹም ወይም ሠራተኛ ንብረት ሲጎድልበት ወይም ሌላ ጥፋት ሲገኝበት ሃብቱ ይወረስ የነበረውን ቅጣት በመለወጥ መቀጫ ይክፈል እንጅ ሃብቱ አይወረስ የሚል ነው፡፡ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ገጽ 91-93፡፡ ሆኖም እነዚህ ነገሮች በቶሎ አለመተግበራቸውን ከተለያዩ ሰነዶች እንረዳለን፡፡

ሆኖም ይህ ከ፲፱፻ ዓ/ም ጀምሮ ያለው ዘመን በዳኝነት ተቋማት ምሥረታ ላይ ያተኮረ ነው። በመሆኑም የመጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለቱ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ሲመሠረቱ የመጀመሪያው ፍርድ ሚኒስቴር ነበር። ንጉሡ በረዳቶቹ በኩል (በጦር አበጋዙ፣ በአፈ-ንጉሡ፣ በጸሐፌ ትዕዛዝና በሊጋባው) ይሠራው የነበረውን ሥራ ሁሉ ለእነዚህ ተቋማት በማከፋፈል በዘመናዊ መልኩ የተደረገ የመጀመሪያው የሥልጣን ክፍፍል የተደረገበት ዘመን ነው።[7]

### ሀ) የፍርድ ሚኒስቴር መመሥረት እና የ፲፪ቱ ወንበሮች ሹመት[8]

"የዳኝነት ሚኒስቴር ደንብ" በደነገገው መሠረት የፍርድ ሚኒስቴር ሲመሠረት የመጀመሪያው የፍርድ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት በጊዜው አፈ-ንጉሥ የነበሩት አፈ-ንጉሥ ነሲቡ መስቀሎ ናቸው። በዳኝነት ሚኒስቴር ደንብ መሠረት፣ ፍርድ ሚኒስትሩ «ያገር ዳኞች ዋና አለቃ ነው፤» በአገሪቱ በየትኛውም ክፍል የሚፈረደውን ፍርድ፣ ራሱም የሚሰጠውን ፍርድ በመዝገብ ያሰፍራል፤ ፍርዱም በፍትሐ ነገሥት[9] አንጻር መሆኑን «በትጋት የሚጠብቅ እሱ ነው።» ይህንንም ለማድረግ እንዲያስችለው «በየሻለቆችም አገር ያሉት ዳኞች ሁሉ የፍርዳቸው መዝገብ ግልባጭ ባመት ወደሱ እየመጣ ይታያል።» በወቅቱ በነበረው የቃላት አጠቃቀም አገር የሚለው ቃል የትውልድ ቀዬ፣ ወረዳ፣ አውራጃ ወይም መላ ኢትዮጵያን የሚመለከት ነበር። በአንድ አውራጃ ውስጥ ያሉ ሁለት ሰዎች አገር የሚለውን ቃል ለወረዳ ሲጠቀሙበት፣ ከሁለት አውራጃ የመጡ ሰዎች ለየመጡበት አውራጃ አገር የሚለውን ቃል ይጠቀሙ ነበር። ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ ግንኙነቶች ደግሞ አገር የሚለው ቃል ኢትዮጵያን የሚያመለክት ነበር። ይህ የቃል አጠቃቀም ለምሳሌ ጣትን፣ እጅን እንዲሁም መላ ሰውነትን አካሌ ብሎ እንደመጥራት የሚቆጠር ቢሆንም፣ ዘመናዊው ሥነ-ትርጉመቃል (semantics) አንድን ቃል (symbol) ለአንድ ነገር (referent) ብቻ መጠቀም እንደሚመረጥ ያስረዳል።

አፈ-ንጉሥ ነሲቡ ቀደም ብሎ በአፈ-ንጉሥነት ያገለገሉ ሲሆን እንደ ንጉሡ ሆነው ከሞት ፍርድ በመለስ ያለውን ማንኛውንም ያገሪቱን የዳኝነት ጉዳይ በብቸኝነት ሲመረምሩና ሲፈርዱ ኖረዋል። አሁን የፍርድ ሚኒስትር በመሆን የአገሪቱን ይግባኞች በሙሉ እንዲያዩ ሲሾሙ፣ ለሥራቸው ረዳት ያስፈልጋቸዋል ተብሎ በ፮ ክፍል (ችሎት)

[7] ሚኒስትሮቹ ከመሾማቸው በፊት የንጉሡ የእለት ክንውን ውሎ ከሰኞ እስከ እሁድ፣ ከጧት ፲፪ ሰዓት እስከ ምሽቱ ፲፪ ሰዓት ድረስ ዐቃቤ ሰዓቱ ከጸሐፌ ትዕዛዙ ጋር እየተቆጣጠረ ለሰዓቱ የተመደበውን ተግባር እንዲከወን ያደርግበት የነበረው የሰዓት ሰንጠረዥ ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ አስፍረዋል። ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ *ዝክረ ነገር፣ ሁለተኛ እትም* (፲፱፻፷፪ ዓ/ም አዲስ አበባ) ገጽ ፷ እስከ ፷፬።

[8] በዚህ ጥናት ውስጥ ቁጥሮች በፊደልም በአኀዝም (በግዕዝ ወይም በአረብ ቁጥር) ይጠቀሳሉ። ይህም የሆነው ምንጭ የሆኑትን ሰነዶች በመከተል ነው። በተለይም የነጋሪት ጋዜጣ አዋጆችና ድንጋጌዎች እንዲሁም ፊደሎቹ የተቀመጡት ራሱ የሚጠቀሰው አዋጅ ወይም ድንጋጌ ውስጥ በተጠቀሱበት አንጻር ነው።

[9] ፕ/ር ፒተር ስትራውስ ለፍትሐ ነገሥቱ የእንግሊዝኛ ትርጉም በጻፉት መቅድም (ገጽ xxi, xxvii) ፍትሐ ነገሥቱ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ላይ ብዙም ተጽዕኖ እንዳልነበረው፣ እንዲያውም በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የፍርድ ሚንስቴር ሲቋቋም ለመጀመሪያ ጊዜ ግልጽ እውቅና እንደተሰጠው ይገልጻሉ። በአንፃሩ ደግሞ ፍትሐ ነገሥቱ ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ ጀምሮ ሥራ ላይ መዋሉን መገመት ይቻላል። ለምሳሌ፣ የ፲፱፻፳፫ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሲወጣም ፍትሐ ነገሥቱን ለማሻሻል እንደሆነ ተደርጎ ነው የተገለጸው። ራሳቸው ባዘጋጁት ትርጉም የተጠቃለለው የሱራሄ ክርስቶስ ጉዳይ ደብረ ሊባኖስ በነበሩት ሊቃውንት ታይቶ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው በፍትሐ ነገሥቱ መሠረት ነበር። የስህተቱ መሠረትም ሊሆን ይችላል ብዬ የማስበው የሕጎች ተፈጻሚነትን በተመለከተ ሁሌም የታተመበትን ሰነድ በመሻት ነው።

ተመድበው የሚሠሩ ፲፪ ወንበሮች (ዳኞች) የካቲት ፲፯ ቀን ፲፱፻ ዓ/ም ተሹመዋል::[10] በዚህ ዘመን «ፍርድ ቤት» የሚባለው ጽንሰ-ሀሳብ አልነበረም:: በፍትሐ ነገሥቱም እንደተመለከተው እንደተቋም የሚታየው ዳኛው ሲሆን አሁን እንደተቋም ስለሚታየው የሥራ ቦታ፣ ስለሚያስችልበት ቦታም ተደንግጓል:: ስለዚህ የወንበሮች መሾም እንደተቋም ምሥረታ ሊታይ የሚችለው ስለዚህ ነው::[11]

አሥራ ሁለቱ ወንበሮች (ዳኞች) በስድስት ተከፍለው ሁለት-ሁለት ሆነው በየችሎቱ የሚቀመጡ ሲሆን የችሎቱ ሰብሳቢ የቀኝ ዳኛው ይመስላል፤ ምክንያቱም የሓሳብ ልዩነት ሲኖር የሚጸናው እርሱ የፈረደው ነው::[12] በዚሁ መሠረት እንደ ቅደም ተከተላቸው ቀኝና ግራ ሆነው የተሾሙት ዳኞች:-

አዛዥ አየለ እና አቶ ይርጉ፣
አቶ ወንደምነህ እና አቶ አረጋኸኝ፣
አቶ ከፈለው እና አቶ ወልደ ዐማኑኤል፣
ግራዝማች ወልደ ዮሐንስ እና ባሻ ክንፌ፣
ቀኛዝማች ኃይለ ሚካኤል ቢልጮ እና ባላንባራስ ሶርሱ፣
አለቃ እስጢፋኖስ እና አቶ ሽብሩ ናቸው::[13]

### ለ) የዳኝነት አሠራርን ስለሚመለከቱ ድንጋጌዎች

ከዚህ በላይ በተመለከተው የመጀመሪያው ዘመን ከዘመናዊ የተቋማት ምሥረታ በተጨማሪ የተቋሙን አሠራር የማደራጀት ክንውኖች ነበሩ:: በዚህ ረገድ ሊጠቀሱ ይገባል ተብሎ የታመነባቸው ሁለት የአሠራር ደንቦች በዚህ ክፍል የተጠቀሱ ሲሆን፣ ከተቋም ምሥረታ ጋር ተጣምረው የተደነገጉት ደግሞ በሚቀጥለው ክፍል ከሌሎች ጉዳዮች ጋር ተዳሰዋል::

መጀመሪያ ሊጠቀስ የሚገባው *ለተፈረደለት ሰው የፍርዱን ግልባጭ ስለመስጠት* በአልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን (በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ) መጋቢት ፳፪ ቀን ፲፱፻፲፬ ዓ/ም የወጣው «ትዕዛዝ» ነው:: ይህ ትዕዛዝ የተፈረደበት ሰው ይግባኝ ለማለት እንዲችል፣ ወይም የሚታሰርም ከሆነ ሲታሰር የፍርዱ ግልባጭ ሊኖረው እንደሚገባ የሚደነግግ ነው:: ከዚህ ዘመን በፊት ይግባኝ ባይ የፍርዱን ይዘት ለይግባኝ ሰሚው ዳኛ

---

10 ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ገጽ ፶፬፣ ፳፰ እስከ ፳፱:: አንዳንድ ጥቃቅን ዝርዝር ጉዳዮች በብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ እና በሌሎቹ ጸሐፊዎች መካከል ልዩነት ሲኖር የብላቴን ጌታን መረጃ ወስጃለሁ::

11 ፍርድ ቤት የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ከመምጣቱ በፊት ተቋም ተደርጎ ይታይ የነበረው ዳኛ ነው:: ስለዳኛ ሹመት ፍትሐ ነገሥቱ በአንቀጽ ፵፫ ከቁጥር ፩ሺ፬፻፲ ጀምሮ ይደነግጋል:: ዳኛ ለመሆን የሚያበቁ አሥራ ሦስት ያህል መጠይቆችን የደነገገ ሲሆን ዘጠነኛው ስለዳኛው ብቃት የሚደነግግ ነው:: በዚሁ መሠረት ከቁ ፩ሺ፬፻፳፬ እስከ ፩ሺ፬፻፳፯ በተደነገገው መሠረት ዳኛ ሆኖ የሚሾመው ሰው (1) የቅዱሳት መጻሕፍትን ይዘትና ትርጉም የሚያውቅ፣ (2) ተቀባይነት ያላቸውን የቅዱሳን አባቶችንና ጉባዔያትን ቃል ማወቅ፣ (3) አባቶች የተስማሙመትንና ያልተስማሙበትን ነገር ለይቶ ማወቅ፣ እና (4) አመሳስሎ መተርጎምን ማወቅ የሚጠበቅበት ሲሆን እነዚህ ለትክክለኛ ዳኝነት እንደሚረዱ ይገልጻል::

12 ለፍርድ ሚኒስትርና ለወንበሮች የተሰጠ ደንብ፣ ፯ተኛ አንቀጽ::

13 ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ገጽ ፳፱ የግርጌ ማስታወሻው:: ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ እነዚህን ወንበሮች በጥንድ በጥንድ ያስቀመጡት እንደተመደቡበትና ይሰሩበት እንደነበረው አግባብ ቀኝና ግራ አድርገው ነው:: የመርስዔ ኀዘን ዝርዝር ትንሽ ለውጥ አለው:: መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ገጽ 50:: አፈ-ንጉሥ ነሲቡ በዚያው ዓመት ሐምሌ ሦስት ቀን ሲሞቱ አለቃ እስጢፋኖስ በዓመቱ ግንቦት ፰ ቀን ፲፱፻፩ ዓ.ም አፈ-ንጉሥነትን ተሹመዋል:: መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ገጽ 59::

በቃል ያስረዳ የነበረው ባላጋራውን/ተከራካሪውን ወገን አስጠርቶ ወይም ፍርዱን የሰጠው ዳኛ እየቀረበ ነበር ::[14]

ይህ በ፲፱፻፲፬ ዓ/ም የወጣው ደንብ የዳኝነት ሥራውን እንዳቀናው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጽሑፋቸው የገለጹ ቢሆንም በጊዜው ተተግብሯል ለማለት አይቻልም::[15] ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ጭሮን (በኋላ አሰበ ተፈሪ) እንዲያለሙ ተሹመው ሂደው ከተማውን አደራጅተው የመንግሥትን ሥራ አስልጠዋል:: በዚሁ መሠረት ወንበሮች ፍርዳቸውን በጽሑፍ አድርገው በሦስት ቀናት ውስጥ እንዲሰጡ በማድረግ ይህን የሥራ አካሄድ አስፈጽመዋል::[16] በዚህ ጊዜ ራስ እምሩ የሐረርጌ አውራጃ እንደራሴ ነበሩ:: በወሎ ስላከናወኑት ተግባር ሲገልጹ እንደሐረርጌው ነበረ ይላሉ:: በኋላም የወሎ አውራጃ የዳኝነት ሥራ መልክ እንዲይዝ የተደረገው ራስ እምሩ ተሹመው ከሄዱ በኋላ በ፲፱፻፳፪ ዓ/ም አካባቢ ነው:: ወሎን በአሥር አስተዳደር ክልሎች ከፋፍለው አበጋዝም (የጦር አለቃ)፣ ወንበርም ጸሐፊም ስለሾሙለት፣ በየአካባቢው በመንግሥት ወንበር የሚሰጠው ፍርድ በቃል መሠጠቱ ቀርቶ የፍርዱ ወይም የብይኑ ግልባጭ እየተሰጠው በሻለቃው ይግባኝ ሲቀርብ ይግባኝ ባዩ የፍርዱን ግልባጭ ከሰጠ በኋላ የይግባኙን ምክንያት በቃል ያስረዳል::[17] ደሴ የሚሰጠው ፍርድም ወደ አዲስ አበባ ለሚመጣው ይግባኝ የፍርዱን ግልባጭ ለረቺና ለተረቺ መስጠት የተጀመረው በዚሁ ጊዜ ነበር::

እንደዚሁም ሁሉ፣ ራስ እምሩ ከወሎ ወደ ጎጃም አውራጃ ተዛውረው በ፲፱፻፳፬ ዓ/ም ሲሾሙ «የዳኝነት ሥራ በፊት በየወረዳው አገር ሁሉ የመንግሥት ዳኞችና ጸሐፊዎች ስለሌሉ ወደ በላይ ዳኛ በጽሕፈት እየሆነ በሚገባ ተሠርቶ የሚተላለፍ የፍርድና የብይን ነገር አልነበረም» ብለዋል::[18] እንደ ወሎ ሁሉ የጎጃምንም የዳኝነት ሥርዓት በ፲፱፻፳፫ ዓ/ም ያደራጁት እርሳቸው ናቸው:: ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት እና ራስ እምሩ የዳኝነት ሥርዓቱን በዚህ ዓይነት መምራት መቻላቸው ከሌሎቹ እንደራሴዎች ወይም ገዥዎች የተሻለ የሥርዓት ግንዛቤ ስለነበራቸው ብቻ ሳይሆን፣ ከራስ ተፈሪ ጋር በነበራቸው ቅርርብ፣ መተማመንና ይህንኑ ተከትሎ በነበራቸው አንጻራዊ የሥራ ነፃነት ጭምር ይመስላል::

በሁለተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚገባው ስለፍርድ ሚኒስትሩና ወንበሮቹ አሠራር የተሰጠው «ደንብ» ነው::[19] ይህ ደንብ ብዙ ነገሮችን የተከለ ወይም ያሻሻለ ሲሆን ዋና ዋና የተባሉት የሚከተሉት ናቸው::

*መጀመሪያ*፣ ወንበሮቹ የሚሰጡት ፍርድ ለፍርድ ሚኒስትሩ ይግባኝ ሊባልበት የሚችል እንደሆነና በዚህ ዓይነት መልኩ ይግባኝ የሚሰማ ከሆነ፣ ሚኒስትሩ ጉዳዩን ካላዩት ሁለት

---

[14] መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ገጽ 50::

[15] ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ*፣ ፩ኛ መጽሐፍ፣ ፪ኛ እትም (ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ፲፱፻፷፫ ዓ/ም) ገጽ ፵፫::

[16] ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም፣ *ኦቶባዮግራፊ (የሕይወቴ ታሪክ)* (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ፪ሺ፫ ዓ/ም) ገጽ 364:: ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት በኋላ በጅሮንድ ነበሩ:: ሆኖም ፊታውራሪ መባልን ስለሚመርጡ ግለ ታሪካቸው በዚሁ የተሰየመ በመሆኑ ይህንኑ በመከተል ፊታውራሪ ብዬ ነው የምጠቅሳቸው::

[17] እምሩ ኃይለ ሥላሴ፣ ገጽ 193::

[18] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 246::

[19] ከዚህ በላይ የተጠቀሰው «ትዕዛዝ» የሚል ሲሆን ይህ ደግሞ «ደንብ» ይላል:: ቃሉን እንዳለ ከድንጋጌዎቹ የተወሰዱ ሲሆን የቃላት ልዩነት ለምን እንደተከሰተ ግልጽ አይደለም:: ሆኖም የተጻፉ ድንጋጌዎች ተደጋግመው በመውጣታቸውና የተጻፈ ድንጋጌን መሠረት ያደረገ ሥራ እየተተከለ ስለነበረ፣ ወጥነቱን ባለማስተዋል የተከሰተ ነው የሚል እምነት አለኝ::

ወንበሮች ጋር በመሆን በሦስት ዳኞች የሚታይ መሆኑን፣ ይግባኙንም የሚሰማው ችሎት የፍርዱን ግልባጭ ሳይቀበል፣ ተጠሪን ሳያስቀርብና ሳይመረምር «የታሰረ ይፈታ፣ የታገተ ይመለስ፣ እጅ ይዛወር እንዳይል» ይከለክላል::[20]

ሁለተኛ፣ የሻለቆች ወንበሮችም ለፈረዱበት ሰው በሁለት ቀናት ውስጥ የፍርዱን ግልባጭ እንዲሰጡ፣ የፍርዱ ግልባጭ በተባለው ጊዜ ያልደረሰ እንደሆነ ሚኒስትሩ ወይም የመንግሥት ወንበሮች የሻለቃ ወንበሮችን ከ፲ እስከ ፶ ብር ቅጣት ሊጥሉባቸው እንደሚችሉና ከዚህም ውስጥ እንደተጉላላው ሰው ማዕረግ ከ፭ እስከ ፳ ብር ሊቀበል እንደሚችል ይደነግጋል::

ሦስተኛ፣ በዳኞች መካከል የሓሳብ ልዩነት የተከሰተ እንደሆነ፣ በወንበሮች መካከል ከሆነ፣ የቀኝ ወንበሩ የሚወስነው የሚጸና ሲሆን፣ የፍርድ ሚኒስትሩ በሚሰየምበት በሚኒስትሩና በወንበሮቹ መካከል ልዩነት ሲከሰት፣ ሚኒስትሩ የፈረደው የሚጸና እንደሆነ ይደነግጋል:: በተጨማሪም ከፍርድ ሚኒስትሩ ፍርድ ይግባኝ ወደ አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ሊቀርብ እንደሚችል ይደነግጋል::

አራተኛ፣ የፍርድ ሥራውን ለማሳለጥ በጊዜው ፲፪ ያህል ጸሐፊዎች ተቀጥረው በየችሎቱ ሁለት - ሁለት የተመደቡ ሲሆን የጸሐፊዎቹም አለቃ አቶ ኃይሌ ሹምዬ ይባሉ ነበር::[21] በደንቡ መሠረት እነዚህ ጸሐፊዎች በፍርድ ሚኒስትሩና በእያንዳንዱ ወንበሮች ክፍል አምስት - አምስት ሆነው እንደሚመደቡ ተንግጓል:: ተግባራቸውም - ሁለቱ ጸሐፊዎች የግራ-ቀኙን ተከራካሪዎች ቃል በእርሳስ መዝግበው፣ ሦስተኛው ይህንኑ ቃል በቀለም በመዝገብ ይገለብጣል:: አራተኛው ጸሐፊ ነገሩን ባጭሩ ጽፎ በወንበሩ ማኅተም ለረቺና ለተረቺ ይሰጣል:: አምስተኛው ጸሐፊ ወንበሩ ባላጋራው ይቅረብለት ብሎ ትዕዛዝ ሲሰጥ የቀላጤውን ደብዳቤ በወንበሩ ማኅተም እያደረገ ይሰጣል::

አምስተኛ፣ በአገሪቱ በሙሉ ያሉት ከተሞችና ወረዳዎች በስድስት ተከፍለው ለስድስቱ ችሎቶች ተመድበው ወር ተራ ወጥቶላቸዋል:: የወንጀል ችሎቱ እስኪቋቋም ድረስ የወንጀል ጉዳዮች ከርስትና ሌሎች የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ጋር በስድስቱ ችሎቶች ይታዩ ነበር:: በኋላም የወንጀል ችሎቱ ራሱን ችሎ አምስት ዳኞች ተሰይመውበት ሲቋቋም ሰባተኛ ችሎት ሆኖ ለራሱ ወር ተራ ወጥቶለታል:: ወር ተራ ማለት አንድ አካባቢ ከየሻለቃው ወንበር (የአውራጃ ፍርድ ቤት) ይግባኙን ለመንግሥት ወንበር እንዲያቀርብ በዓመቱ የወራት ጊዜ ውስጥ ለአውራጃው የተመደበለት የጊዜ ሰንጠረዥ ነው:: ይህ ወር ተራ የወጣው የአካባቢውን ርቀት፣ መልክዓምድሩን፣ የአካባቢውን የእርሻ ሥራና የመኸር ወራት ወዘተ መሠረት በማድረግ ነው:: ለምሳሌ ጎንደር፣ በጌምድር፣ ቋራ፣ ወገራ፣ ስሜን ወዘተ ወር ተራ ሚያዚያ ነው:: በአንጻሩ አዲስ አበባ በሰኔ ወር የተመደበ ሲሆን በየሳምንቱ ሐሙስ መቅረብ እንደሚችል በተጨማሪ ተመልክቶለታል::[22]

በእያንዳንዱ ችሎት ከአሥር እስከ ሃያ ሰው በቀን ማስተናገድ ይበቃል ተብሎ ስለተተመነ[23] ከሻለቃ ዳኞች ወደ መንግሥት ወንበር ይግባኝ የሚለው ሰው «ለጫኺ

[20] ሚኒስትሩ ማክሰኞና ቅዳሜ የሚሰማውና ከወንበሮቹ ውሳኔ የሚቀርበውን ይግባኝ በዚህ ደንብ «ሰበር» ተብሎ ተጠቅሷል:: አሥራ አራተኛ አንቀጽ:: በዚህ ዘመን ሰበር የሚለው ቃል አሁን ይግባኝ የሚለውን ቃል የሚተካ ነው:: ለምሳሌ በአሰበ ተፈሪ አውራጃ ቀኛች በላቸው የቀኝ ወንበር ሲሆኑ ሰበሩ ይታይ የነበረው በፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት እንደነበረ ገልጸዋል:: ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም፣ ገጽ 383::

[21] መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ገጽ 50::

[22] ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ገጽ ከ፹፫ እስከ ፺፭:: መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ገጽ 32930::

[23] አሥራ ዘጠነኛ አንቀጽ::

ጠባቂነት ወደ ተሾመው ሰው» (አስተናባሪው) ዘንድ እየቀረበ የችሎት መቅረቢያ ቀላጤ ይወስዳል። በቀላጤውም ላይ «የወንበሩን ስም፣ የመጣበትን ቀንና ወር፣ ስሙንና አገሩን፣ የባላጋራውንም አገርና ስም አጽፎ እየተቀበለ በተራው ይነጋገራል»።[24]

### ሐ) ስለወንጀል ችሎት መቋቋም

ራስ ተፈሪ መኮንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆነው አውሮፓን ጎብኝተዋል። ራስ ተፈሪ በጉብኝታቸው ወቅት የታዘቡት አንዱ ነገር የወንጀል ችሎት ለብቻው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረጃ መቋቋምና መሥራቱን ነው። በመሆኑም እንደተመለሱ አምስት ዳኞች ያሉበት የወንጀል ችሎት በሰኔ ፲፱፻፲፱ ዓ/ም አቋቁመዋል።[25]

የዚህ ችሎት መቋቋም መሠረታዊ ውጤቶች ብዙ ናቸው። በመጀመሪያ «ፍርድ ቤት» የሚለውን የተቋም መጠሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀምነው ለዚህ ችሎት ነው፤[26] ሁለተኛ ይህ ችሎት የሚሰየመው በአምስት ዳኞች ሲሆን የመጀመሪያዎቹ ዳኞች (1) ደጃች መስፍን ገመቹ የመጀመሪያው የፍርድ ቤቱ ፕሬዚደንት (ሰብሳቢ ዳኛ)፣ (2) ልጅ ባንጃው ናደው፣ (3) አቶ ወንዴ፣ (4) አለቃ ዳኜ፣ (5) አለቃ ሠርጹ ኃይሌ የተባሉ ናቸው።[27]

ይህ ወቅት የዳኝነት ሥልጣንን በመጠኑ ለመደንገግ የተሞከረበት ነው፤ በመሆኑም በሞት ከሚያስቀጡ ወንጀሎች በመለስ (የንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን ስለሆነ) ከፍተኛ ወንጀሎች በሙሉ የግድያ ወንጀሎች፣ የቤት አቃጣይ፣ የስርቆት፣ ውንብድናና እምቢተኝነት፣ የመንግሥትን አዋጅ የሚጥሱ ሁሉ ጉዳያቸው በዚህ ችሎት መታየት ጀመረ።[28] በመመሪያው መሠረት ከአንድ እስከ ስድስት ወር እሥራት የሚያስቀጣ፣ በገንዘብም ቢሆን ከዐሥር እስከ መቶ ብር የሚያስቀጣ ሲሆን ችሎቱ ቅጣቱን መወሰን ይችል ነበር። ቅጣቱ ከዚህ በላይ ከሆነ ግን ነገሩን ለንጉሥ ችሎት እያቀረበ የሚገባው ቅጣት ይፈረድበት ነበር። ፍርዱ የሚሰጠው በድምጽ ብልጫ ነበር።[29] ሌሎች ተራ ወንጀሎች ደግሞ ለሻለቃ ዳኞች የተሰጡ ናቸው።[30] ይህ አሠራር የ፲፱፻፳፫ ዓ/ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እስከሚወጣ ድረስ የጸና ነበር።

### መ) የነፍስ-ገዳይ ጉዳይ ምርመራና አሰማም

በተደጋጋሚ እንደተመለከተውና በቀረቡትም የፍርድ ሂደቶች እንደታየው የነፍስ ግድያ ወንጀል በንጉሡ ችሎት የሚታይ፣ እንዲሁም ምርመራውና ክስ መስማቱ በአንድ ላይ በችሎት የሚከናወን ነበር። ራስ ተፈሪ የወንጀል ችሎቱን አቋቁመው ስለ ነፍሰ ገዳይ ምርመራና ክስ አሰማም የሚደነግገውን ደንብ አወጡ። በዚህ ደንብ መሠረት ምርመራው የሚከናወነው በሻለቃ ወንበር ወይም በአውራጃ ገዥው ሲሆን ጉዳዩ ለንጉሡ ችሎት

---

[24] አሥራ ሰባተኛ አንቀጽ። ወረፋው ችግር ስለሆና ሰውም ከሩቅ አገር በመምጣት ከፍተኛ እንግልት ስለሚገጥመው የችሎት አቀራረቡን ያዛቡ ሠራተኞች ለመጀመሪያው ሦስት ጥፋት ፲፣ ፳ እና ፶ ብር በቅደም ተከተል ይቀጡና በአራተኛው ጥፋት ከሥራ ይሰናበታሉ። ዐሥራ ስምንተኛ አንቀጽ።

[25] መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ገጽ 329-30።

[26] በተለይም ስለነፍሰ ገዳይ ነገር በተሰጠው ደንብ ውስጥ «ወንጀል ፍርድ ቤት» እና «ወንጀል ቅጣት ፍርድ ቤት» በማለት ይጠቅሰዋል።

[27] ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ገጽ ፹፰።

[28] ስለ ነፍሰ ገዳይ የተሰጠውን ደንብ በግልጽ የነበረውን አሠራር ይደነግጋል።

[29] የወንጀሉ ችሎት ጸሐፊዎች የተመደቡለት ሲሆን የጸሐፊዎቹ አለቃ በቀለ ዛማኔል የተባለ ብልህ የእንጦጦ ራጉኤል ደብተራ ነበር ተብሏል። መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ገጽ 329-30።

[30] ዝኒ ከማሁ።

ሲቀርብ ምርመራው በስሎ ነው። በዚህም መሠረት ደንቡ የግድያን ወንጀል የአውራጃው ገዥና ወንበሩ አራት የታወቁና የታመኑ ነባሪዎችን ይዘው መመርመር እንዳለባቸው ይደነግጋል።

የምርመራውም ሂደት መጀመሪያ የሚች ዘመዶች ይጠየቃሉ፤ ቀጥሎ ገዳዩ ይጠይቃል። መጀመሪያ ለየብቻ፣ ቀጥሎ በአንድ ላይ ያነጋግሯቸውና የሚካካዱ ከሆነ ምስክሮች ለየብቻ ይሰማሉ። ይህ ሁሉ በዝርዝር ተጽፎና በሦስት ግልባጭ ማንተም ተደርጎበት አንዱ በአውራጃው ዳኛ ጽ/ቤት፣ ሁለተኛው በሚች ወገኖች፣ ሦስተኛው በገዳዩ እጅ ሆኖ «ወደ ወንጀል ቅጣት ፍርድ ቤት» ይላካል። የአውራጃው ዳኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የወንጀል ቅጣት ፍርድ ቤት ይሙት በቃ ፍርድ መስጠት አይችሉም።

ይህ ከአውራጃው ዳኛ የመጣው ጽሑፍ በችሎት ከተነበበ በኋላ የጎደለ ካለ በዚሁ ችሎት ተጨማሪ ምርመራ ተደርጎ ይሟላና ወደ ንጉሠ ነገሥት ችሎት ይቀርባል። ምርመራው ከተሟላ በኋላ በንጉሡ ችሎት እንደ ዐቃቤ ሕግ ሆኖ «የወህኒው ዘበኛ ሹም ይህ አሁን የተነበበው ቃል ያስሞትኻልና ሙት ብሎ ይፋረደዋል»።

በችሎት የተቀመጡት ፈራጆች (ዳኞች) እና ፍትሐ ነገሥቱ ይሙት በቃ ብለው የፈረዱ እንደ ሆነ ይኸው ይፈፀማል።[31] ነፍሰ ገዳዩ በግፍና በተንኮል መግደሉ ከተመሰከረበትና ሞት ቅጣት ከተፈረደበት፣ በፍጥነት ይገደላል እንጂ «ሁለት ቅጣት እንዳይሆንበት ብዙ ቀን ታስሮ አይቆይም»።

**ሠ) ቅጣት አወሳሰንና አፈጻጸም**

በተለያዩ ሰነዶችና ድንጋጌዎች እንደተመለከተው፣ በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን መካከል የነበረው ቁርኝት ሥር የሰደደ ስለነበረ በ«ኃጢአት» እና በ«ወንጀል» መካከል የይዘት ልዩነት አልነበረውም። ማንኛውም ሰው አንድን የሚከሰስ ሰው ይዞ ለችሎት ሲቀርብ የቀረበውን ሰው «ኃጢአት» ወይም «ወንጀል» ለዳኛው (እንደነገሩ ሁኔታ ለንጉሠ ነገሥቱ) ይገልጻል። በመሆኑም በንጉሡ ፊት አንድ ሰው ተከሶ ሲቀርብ ንጉሡ የሚጠይቁት «የዚህ ሰው ኀጢአት ምንድን ነው?» ብለው ነው። የወንጀል ቅጣት ንሥሐ ገብቶ ይቅርታን ለማግኘት የሚቻልበት ሂደት ተደርጎ ስለሚወሰድ ያለ ቅጣት ንሥሐ የለም፤ ያለ ንሥሐም ይቅርታ የለም። የሞት ቅጣትም ቢሆን ምድራዊውን ቅጣት በመቀበል ከዘላለማዊ ሞት መትረፍ ይቻላል ተብሎ ይታመን ነበር።[32]

ከዚህም በተጨማሪ በወንጀልና በፍትሐ ብሔር ክስ መካከል ብዙም ልዩነት ስላለነበረው ክሱን የሚያቀርበው የግል ተበዳይ ወይም ቤተሰቦቹ ነበሩ። የግድያ ወንጀል ሲሆንና ተበዳይ ዘመድ ከሌለው ወይም ጉዳዩን የሚከታተል ከሌለ የወህኒ አዛዡ የተከሳሹን ወንጀል ለንጉሡ ችሎት ያስረዳል። በቀደመው ዘመን ውሸት ነገር መናገር በጣም አስነዋሪ ስለነበረ፣ ብዙ ጊዜ በፍሬ ነገር ላይ መሠረታዊ ክርክር አይደረግም። ክርክሩ በፍሬ ነገሩ

[31] ፍትሐ ነገሥቱ በአንቀጽ ፵፯ ቁጥር ፩ሺ፯፻፯ እና ፩ሺ፯፻፱ ሥር «ባለደም ገዳይን ሊገድል ይገባዋል። … ለባለደም ጠላቱን በእጁ ሊገድል አይገባውም። ይገድለው ዘንድ ከዳኛ ያድርሰው እንጅ። …እንደ ኃጢአቱ ይፈርድበት ዘንድ» በማለት ይደነግጋሉ። በዚህ መሠረት ለምሳሌ የጎጃሙ ደ/ጃች ወዳጅ ባለቤታቸውን በቅናት ምክንያት ገድለው በንጉሡ ችሎት ጥፋተኛ ተብለውና ሞት ተፈርዶባቸው ለሚች ቤተሰብ ተሰጥተው ነሐሴ 18 ቀን 1897 ዓ/ም (በጥይት) ተደብድበው ተገድለዋል። አቃቂ መድኃኒ ዓለም ተቀብረዋል። መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ገጽ 29።

[32] ዣን ግራቨን «የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ»፣ *የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት* ቅጽ ፩ ቁጥር ፪ (፲፱፻፶፯ ዓ/ም) ገጽ 214-15፣ ፍትሐ ነገሥቱ በተለያዩ ክፍል ለሁሉም ወንጀሎች (ኃጢአቶች) መንፈሳዊ ቅጣት ንሥሐ ያዛል። የግድያ ወንጀሎችን በተመለከተ በአንቀጽ ፵፯ ሥር ከቁጥር ፩ሺ፯፻፲፫ ስለመንፈሳዊ ቅጣት ይናገራል - እርሱም በዋናነት ንሥሐ መግባት ነው።

የሕግ ውጤት ላይ ነው። በዚህና በሌሎች ምክንያቶች የችሎት ጊዜው በአብዛኛው በአንድ ማለዳ የሚያልቅ ሆኖ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ቅጣቱ ወዲያውኑ ይፈጸማል።

በጊዜው የነበሩ የቅጣት ዓይነቶች የተለያዩ ሲሆኑ[33] ዳኞች የተከሳሹን ወንጀለኛነት ካረጋገጡ በኋላ ቅጣቱን የሚያውቀው እርሱ ነው ተብሎ ስለሚታመን ለቅጣት ወደ አገረ ገዥው ነበር የሚልኩት። ለምሳሌ በወላይታ አውራጃ የእስረኛ ጠባቂዎች በስካር ምክንያት እስረኛ አመለጣቸው። በዚሁ ምክንያት የጠባቂዎቹ ጉዳይ ለፈራጆች ቀርቦ ሁሉም በጠባቂዎቹ ላይ «ትቀጣላችሁ፤ ቅጣቱን ግን የበላይ ያውቃል» እያሉ «እንደ ቆየው የፍርድ ልማድ እየተቹ» ፈረዱባቸው። ከሳሹ ራሳቸው የወላይታው ገዥ የነበሩት ደጃች በየነ ወንድማገኝሁ ነበሩና ጠባቂዎቹ እያንዳንዳቸው አርባ ጅራፍ እንዲገረፉ ወሰኑ።[34]

የ፲፱፻፳፫ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከወጣ በኋላ የፍርድ ቤቶቹን አሠራር መሠረታዊ በሆነ መልኩ ለውጦታል፤ ምክንያቱም ዳኛው ጥፋተኝነቱን ከፈረደ በኋላ ቅጣቱን እንዲወስን አስችሎታል።[35] ይህም የሆነበት ምክንያት ሥልጣኑ ስለተሰጠው ብቻ ሳይሆን ቅጣቱ በወንጀሉ አንጻር መደንገጉ ሲሆን፣ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችም ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ተደንግገዋል። በ፲፱፻፳፫ቱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተደነገጉና ትርጉም የተሰጣቸው የቅጣት ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፦

1. የሞት ፍርድ - በንጉሥ ችሎት ብቻ የሚሰጥ ፍርድ፣[36]
2. የግርፋት ፍርድ - ለሞት ፍርድ የማያደርስ ትልልቅ ወንጀልን በተመለከተ የሚጣል ሆኖ፣ ለሞት እንዳይዳርግ በጥንቃቄ የሚፈፀም ቅጣት ነው፤ ወንጀሉ ቀላል የሆነ እንደሆነ የግርፋት ቅጣቱ ወደ ገንዘብ የሚቀየር ሲሆን አንድ ግርፋት የሚታሰበው በአምስት ብር ነው።
3. የእሥራት ፍርድ
4. የመቀጫ ገንዘብ ፍርድ - መቀጮ የተጣለበት ሰው ለመክፈል ዋስ ጠርቶ ይፈታል። በእስራት የሚቀየር ቢሆን ቅጣቱ ከአንድ ዓመት መብለጥ የለበትም።
5. ግዞት[37] - በንጉሥ ችሎት ብቻ የሚፈረድ፣
6. የመወረስ ፍርድ - ርስቱ እንዳይወረስ በንጉሡ ከታወጀው በቀር (ለምሳሌ ርስት መውረስ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት በአዋጅ ተከልክሏል) ወንጀል ሲሰራ በእጁ የተገኘ መሣሪያ፣ የተሰረቁ ዕቃዎች እንዲወረሱ የሚል ፍርድ፣

[33] በፍትሐ ነግሥት ውስጥ በወንጀልና በፍትሐ ብሔር ተጠያቂነት መካከል ብዙ ልዩነት አላደረገም። ሆኖም በንጉሡ፣ በቤተ ክርስቲያንና በእምነት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስቀጡ ሲሆን፣ ቅጣቱ የወንጀሉን ነውረኛነት ለማመልከት ሲባል፣ በሰይፍ መቀላት፣ በድንጋይ መወገር፣ በእሳት መቃጠል፣ አፍንጫን መቆረጥ፣ ራስን መላጨት፣ ግዞት፣ ወዘተ የተደነገገ ሲሆን ለተራ ወንጀሎች ግን ካሣ መክፈል ዋና የቅጣት ዓይነት ነበር።

[34] መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ገጽ 248-49።

[35] ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ገጽ ፵፯።

[36] በዘመናዊ የችሎት አነጋገር «ፍርድ» ለጥፋተኝነቱ የሚሰጥ ሲሆን «ውሳኔ» ደግሞ የሚመለከተው ቅጣቱን ነው። በቀደመው ዘመን ወንጀል የመለኮት ሕግን መተላለፍም («ኀጢአት») ስለነበረ ቅጣትም ሃጢአትን ማስተሰረያ ተደርጎ ስለሚቆጠር «ፍርድ» የሚለው ቃል የሚጣለውን ቅጣት ነበር የሚገልጸው። ሆኖም አሁንም ድረስ ክብደቱን ለመግለጽ ይመስላል «የሞት ቅጣት» ሳይሆን «የሞት ፍርድ» እንላለን።

[37] ከአንድ አካባቢ ወደሌላ አካባቢ ተልኮ በዚያ ተገድቦ እንዲኖር ወይም ወደ አንድ አካባቢ እንዳይደርስ ተገድቦ እንዲኖር መፍረድ ማለት ነው።

7. የእጅ ጠብቅ ዋስ መስጠት ፍርድ - ተጨማሪ ወንጀል ወይም ሁከት እንዳይፈጥር የሚጠራው ዋስ ሲሆን፣ ዋስ እስከሚጠራ ለስድስት ወር ያህል ይታሠራል፣ ዋስትናውም የሚጸናው ለሁለት ዓመት ብቻ ነው።

እስራትና የግዞት ቅጣት የሚጣለው መኳንንቱና መሳፍንቱ በንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣንና ጥቅም ላይ ጥፋት ፈጽመው ወይም ለንጉሡ ሥልጣን አስጊ ሆነው ሲገኙ ነው።[38] ለዚህም ዋናው ምክንያት ለዘወትር የሚያገለግል እስር ቤት አለመኖር ነው። ለምሳሌ ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ንግሥቲቱን እጅ አልነሱም ተብለው በፊታውራሪ ገብረ ማርያም ቤት (በፊታውራሪ ገብረ ማርያም ሁለት አገልጋዮች የፈረቃ ቁራኛ) አራት ወራት ተኩል ያህል ታስረዋል።[39] መደበኛው ዜጋ እንደ ስርቆት ያለ ተራ ወንጀል ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ፣ በአብዛኛው የሚጣለው የግርፋት ቅጣት ነው።[40]

የሞት ፍርድ መፍረድ ለንጉሡ ብቻ የተወሰነ ሥልጣን እንደሆነ በተደጋጋሚ ተገልጧል። ሆኖም በተለያዩ አካባቢዎች የነበሩ ነገሥታት የሞት ፍርድ ሲፈርዱ ነበር። ለአብነት ንጉሥ ሚካኤል በወሎ፣ ደሴ ችሎት ተሰይመው፣ በአፈ-ንጉሣቸውና በወንበሮቻቸው በመታገዝ የሞት ፍርድ ሰጥተው ወዲያው መፈጸሙን የራስ እምሩ ጽሑፍ ያስረዳል።[41] አካሄዱም አዲስ አበባ በንጉሠ ነገሥቱ ግቢ እንደሚደረገው እንደነበር ገልጸዋል። ራሳቸው ራስ እምሩ የጎጃም እንደራሴ ሆነው በተሾሙ ጊዜ የሞት ፍርድ ባለመፈጸሙ ምክንያት ወንጀል ስለመበራከቱ ጠቅሰው በጅራፍ እንዲገረፉ ማድረጋቸውን ገልጸዋል።[42] በኋላ ግን በሸንጎ በዳኝነት እየታየ የተመሰከረባቸው ነፍሰ ገዳይ ወንበዴዎች በጠቅላላው አሥራ ስምንት የሚሆኑ እየተፈረደባቸው መገደላቸውን ጠቅሰዋል።[43]

### ረ) የይግባኝ ሥርዓትና ሂደትን በተመለከተ

የይግባኝ ቅሬታ አቀራረብና አሰማም የሥልጣን ተዋረድ በአግባቡ የተደራጀን የዳኝነት ሥልጣን ተዋረድ መሠረት ያደረገ ሊሆን እንደሚገባ ግልጽ ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ የይግባኝ ዳኝነት የሥልጣን ተዋረድ የአስተዳደሩን አደረጃጀት መሠረት ያደረገ ይሆናል ተብሎ ይታመናል። ነገር ግን፣ እስከ ፲፱፻፳፬ ዓ/ም ድረስ የነበረው የአስተዳደር አደረጃጀት ይህ ነው የሚባል ወጥነት ያለው አይደለም።[44] የአካባቢው ነገሥታት ወይም

---

[38] ለምሳሌ አፍቀራ የተባለው እስር ቤት፣ በመንዝ አውራጃ የሚገኝ ሲሆን የጎጃሙ ገዥ ራስ በዛብህ 1883 ዓ/ም፣ በኋላም ደጃች ስዩም በ1894 ዓ/ም፣ ራስ ጉግሳ ወሌ እስክ 1908 ዓ/ም ታስረውበት ነበር። ሸንኩርት የተባለ ዋሻ፣ ሰላሌ አውራጃ የሚገኝ ሲሆን የትግሬው ገዥ ደጃች አብርሃ ከ1902-04 ዓ/ም ታስረውበት የነበረ ነው። ፍቼ - ልጅ እያሱ በፍቼ ለአሥር ዓመታት ያህል ታስረውበት የነበረው ቦታ ራሱን ችሎ የተሰራ ቤት ነበር። እንዲሁም በቤተ መንግሥቱ ውስጥ እሥር ቤት ስለመኖሩ ሰነዶች ያመለክታሉ። ልጎት የተባለ አምባ፣ በወሎ የሚገኝ ፊታውራሪ ታዬ ጉልላቴ በ1902 ዓ/ም፣ ራስ አባተ በ1909 ዓ/ም ታስረውበት የነበረ ነው። ደንዲ የተባለ እስር ቤት፣ ጨቦ ውስጥ የነበረ ንጉስ ሚካኤል 1909/1910 ዓ/ም ታስረውበት የነበረ ነው፤ ጅበላ፣ በጎጃም የሚገኝና ባሻ ደቻሳ ታስረውበት የነበረ ነው።

[39] ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም፣ ገጽ 388-95።

[40] መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ገጽ 42።

[41] እምሩ ኃይለ ሥላሴ፣ ገጽ 49-50። ከቀረቡት ስምንት ተከሳሾች ውስጥ አምስቱ ሞት ተፈርዶባቸው ወዲያው «በጠመንጃ ተደብድበው ሞቱ»።

[42] ዝኒ ክማሁ፣ ገጽ 252።

[43] ዝኒ ክማሁ፣ ገጽ 257።

[44] ወጥነት ያለውና ምክንያታዊ የሆነ የአስተዳደር አደረጃጀት ለማስፈን ከፍተኛ ጥረት እንደነበረና ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ጨርጨርና አሰበ ተፈሪን ለናሙና እንዴት እንዳደራጁ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል። ባሕሩ ዘውዴ፣ *ፋና ወጊ የለውጥ አቀንቃኞች በኢትዮጵያ፤ በሃያኛው መቶ ዓመት መባቻ*

እንደራሴዎች የሚሾሙበት ከላይ ያለው አደረጃጀት በአብዛኛው፣ ለረጅም ጊዜ አውራጃ ተብሎ ይጠራ ነበር:: ለምሳሌ ደጃች ተፈሪ (በኂላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ /ቀኃሥ) በ፲፱፻፪ ዓ/ም የአባታቸውን አገር ሐረር አውራጃን በእቴጌ ጣይቱ ተሹመው መሄዳቸውን ይገልጻሉ:: ለአስተዳደር እንዲያመች ሐረርጌ አውራጃን፣ ጨርጨርን፣ ጅጅጋንና ኦጋዴንን ጨምሮ በ፲፪ ታላላቅ አውራጃ እንደከፈሉት ጠቅሰዋል:: ቆይቶም በራስ ተፈሪ ተሹመው የሄዱት ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት በጨርጨርና በጅጅጋ አውራጃዎች ሥር የሚገኙ ወረዳዎችን ይዘረዝራሉ::[45] ራስ እምሩም ያስተዳድሩት የነበረው ሐረርጌ አውራጃ በሥሩ የነበሩት ወረዳዎች እንደነበሩ ተመለክቷል::[46] ከአውራጃ ሥር ያለው የአስተዳደር ተዋረድ ወረዳ ነው:: ሆኖም ይህ አደረጃጀት ወጥ አይመስልም፤ ምክንያቱም ከአውራጃ ሥር አውራጃ አለ፤ ከወረዳ ሥር ደግሞ ወረዳ አለ::

ለምሳሌ ራስ እምሩ ራሳቸው የወሎ እንደራሴ ሆነው ሲሾሙ የወሎ አውራጃን ለግብር ጉዳይ መጀመሪያ በሦስት የአገር ክፍል ከፈሉት - ወረሂመኑ፣ ቃሉ እና ተሁለ ደሬ ብለው:: እነዚህን ቦታዎች ቆየት ብለው ሦስቱ «ወረዳዎች» ብለው ይጠቅሷቸዋል:: ሆኖም ሌሎቹ ወረዳዎች በነዚሁ ወረዳ በተባሉት ሦስት አደረጃጀቶች ሥር የሚጠቃለሉ መሆናቸውን ያመለክታሉ::[47] ቆይተው ለአስተዳደር ጉዳይ ግን በአሥር ክፍል ከፍለው አበጋዝ (የወታደር አለቃ)፣ ወንበር (ዳኛ) እና ለየሥራው ዘርፍ ጸሐፊዎች ተሾመላቸው::[48] ይህ አከፋፈል ከሥሩ ወረዳዎች እንዳሉ የሚያመለከት ነው::

እንደዚሁም ሁሉ የጎጃም እንደራሴነት ተሹመው ፲፱፻፳፫ ዓ/ም ሲሄዱ ጎጃምን አውራጃ አላሉትም:: ሆኖም አገሩን በአሥራ አንድ ክፍል የከፈሉት ሲሆን ለእያንዳንዱ ክፍል አገረ ገዥ ከወንበሮች ጋር ሹመውለታል:: እነዚህ አሥራ አንድ የአገሩ ክፍሎች የተለያዩ ወረዳዎችን በውስጣቸው ይይዙ እንደነበረ ራሳቸው ራስ እምሩ ጠቅሰዋል::[49] ሆኖም ይህ እላይ ባለው በአውራጃው እና እታች ባለው በወረዳው መካከል ያለው አደረጃጀት ግልጽ አይደለም:: አልፎ አልፎ የቃላት አጠቃቀሙ ከቃላት እጥረት አንጻር በተከሰተ ቸልተኝነት ሥራ ላይ ውለዋል ከሚያሰኝ በቀር ለወረዳም ሆነ ለአውራጃ የሚሾመው ሹም በንጉሠ ነገሥቱ ስለሆነ ይታወቃል ተብሎ ይታመናል::

የዳኝነት አደረጃጀቱም የአስተዳደር አደረጃጀቱን ተከትሎ የመጣ በመሆኑ ከየቀበሌው ይግባኝ ወደ ወረዳ፣ ከወረዳ ደግሞ (ወደ ተመደበው ክፍል ወይም እንደነገሩ ሁኔታ) ወደ አውራጃ (የሻለቃ ፍርድ ቤት)፣ ከሻለቃ ፍርድ ቤት ወደ መንግሥት ወንበር፣ ከመንግሥት ወንበር በሰበር ወደ ሚኒስትሩ (የአፈ-ንጉሡ) ችሎት፣ ከዚያም ዙፋን ችሎት እያለ የሚዘልቅ ነው::

ይህ ተቋማዊ አደረጃጀት የዳኝነት ተዋረዱን የሚያመለክት ቢሆንም፣ የይግባኝ አሰማሙ ሂደት ግን ይህን ተዋረድ መከተል እንዳለበት የሚያስገድድ ደንብ ስለመኖሩ የሚያመላክት ነገር የለም:: ከዚህም ባለፈ ለምሳሌ የአውራጃዎቹ ብዛት 41 እንደነበሩ ተጠቅሷል:: ሆኖም ይህ ዝርዝር ከመንግሥት ወንበር ወር ተራ ሰንጠረዥ ጋር የተጣጣመ አይደለም:: የወር ተራ ሰንጠረዡ ብዛት ያላቸውን ቦታዎች ይዘረዝራል፤

---

(አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ 2013 ዓ/ም) ገጽ 163-75፤ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም፣ ገጽ 220-28፣ 259::

[45] ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም፣ ገጽ 363-64፣ 354-55::

[46] እምሩ ኃይለ ሥላሴ፣ ገጽ 92::

[47] ዝኒ ክማሁ፣ ገጽ 164::

[48] ዝኒ ክማሁ፣ ገጽ 191-92::

[49] ዝኒ ክማሁ፣ ገጽ 244-46::

ከነዚህ የሻለቃ ፍርድ ቤቶች ይግባኙ ወደ መንግሥት ወንበር ሊመጣ እንደሚችል በራስ ተፈሪ የወጣ ደንብ ነው።

ከዚህም ባለፈ ኅዳር ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ/ም የወጣው አዋጅ የይግባኝ ሥርዓቱን ቅጥ አስይዞታል።[50] በዚህም መሠረት ይግባኝ ባይ በቀጥታ ወደ ወንበር መምጣቱ ቀሪ ሆኖ በየቦታው እንደተለመደው በየዳኛው ከተፈረደ በኋላ የፈረደው ዳኛ ግራ-ቀኙን አያይዞ ከየወረዳው ዳኛ ጉዳዩን ያስረዳል። ይህም ፍርድ ይግባኝ የሚሰማበት ቦታ ከአንድ ቀን የእግር መንገድ በላይ እንዳይሆን ሆኖ በአማካይ ቦታ በወረዳ ገዥ ወይም በምስለኔ እንዲሆን ይደነግጋል። በወረዳው ዳኛ የሚሆነው ሰው ለድሀ የሚያዝን፣ እውነት የሚናገር፣ ሥርዓት የሚያውቅ ተመርጦ ምሎና ተገዝቶ እንደሚሾም ይደነግጋል። በአውራጃው የሚሾመው ዳኛ ግን የሚረዱት የታመነ ጸሐፊና አጋፋሪ የሚያስፈልገው እንደሆነ ሲደነግግ፣ ማናቸውም ሥራ በመዝገብና በካርኔ በጥንቃቄ እንዲሠራ ይደነግጋል።

የአውራጃው ዳኛም ግራ-ቀኙ የሚመርጧቸው ሁለት-ሁለት እማኞች ባሉበት ይፈርዳል። በፍርዱ ላይ ይግባኝ የተባለ እንደሆነ ዳኛው፣ እሱ ራሱ፣ አራቱ እማኞች፣ ጸሐፊውና አጋፋሪው የፈረሙበትን ፍርድ ለአገረ ገዥው ያሳያል። አገረ-ገዥው ወይም ወንበሩ የፍርዱን ግልባጭ አይቶ ባላጋራውን (መልስ ሰጪውን) የሚያስቀርብ ሲሆን በግራ-ቀኙ በሚመረጡ እማኞችን ይዞ ፍርድ ይሰጣል።[51] አንደኛው ወገን ይግባኝ ማለት የፈለገ እንደሆነ አምስቱም የፈረሙበት ፍርድ ይሰጠውና «ወደ መንግሥት ችሎት» ለአውራጃው የተመደበለትን የጊዜ ሰንጠረዥ መሠረት በማድረግ ይቀርባል። የይግባኝ ጊዜው የሚገዛው በወር ተራው ሰንጠረዥ መሠረት ሲሆን ይግባኙ ሳይቀርብ ይህ ወር ተራ ያለፈ እንደሆነ ምን ውጤት እንደሚያስከትል አልተመለከተም።

በመንግሥት ችሎት ወንበሮቹ (ሁለቱ ዳኞች)፣ በግራ-ቀኙ የሚመረጡ ሁለት-ሁለት እማኞችና በተጨማሪ የሚመደቡትን ጨምሮ በጠቅላላው ስምንት እማኞች ባሉበት ጉዳዩ ይታያል። የተፈረደበት ወገን በወንበሮቹ ፍርድ ቅር የተሰኘ እንደሆነ ነገሩ ቅሬታው ይታያል። ከዚህ በኋላ ጉዳዩ የሚታየው በንጉሠ ነገሥቱ ችሎት ነው። በዚህ ሂደት ሁለት ነገር ማየት ተገቢ ነው። አንደኛው የይግባኙ ሂደት ያልተገደበ ቢመስልም፣ ይህን የመሰለ ቅርጽ ይዞ እንዲፈስና እልባት መቋጫ እንዲያገኝ የተደረገው በዚህ አዋጅ ምክንያት ነው። ሁለተኛው በይግባኝ ሂደቱ በሙሉ የዳኝነት የሚከፈል ሲሆን፣ በሹም-ሺር ጊዜ የተሻረው ዳኛ (አገረ ገዥ) ለተሾመው ዳኛ (አገረ ገዥ) ሲሰራበት የነበረውን ሰነድ በሙሉ አስረክቦ ደረሰኝ እንዲቀበል ይደረጋል።

### ሰ) የሕግ አወጣጡ መዘመን

ንጉሠ ነገሥቱ ሕግ የማውጣት ሥልጣናቸውን ተጠቅመው ተቋማትን መሠረቱ፤ የሚሠሩበትንም ሕግ አወጡ። ይህ የመጀመሪያው እርምጃ ነበር። ሕግ የማውጣት ሥራን በሚመለከት፣ የፍርድ ሚንስቴርን ያቋቋመው አዋጅ ከአራት አናቅጽ ያልበለጡ ድንጋጌዎች ነበሩት። በሂደት የሕግጋቱ ይዘትና አደረጃጀት እየተሻሻለና እየሰፋ መጣ።[52]

[50] ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ከገጽ ፺ እስከ ፺፪።

[51] ዳኞች ችሎት ይሰየሙ የነበረው አደግድገው ነው። ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም፣ ገጽ 385። ማደግደግ ማለት የሸማውን ማጣፊያ በወገብ ጠበቅ አድርጎ አስሮ እጅን ነፃ አድርጎ ለሥራ ዝግጁ በሆነ መልኩ ተግባርን ማከናወን ነው።

[52] ለምሳሌ ከኢጣሊያ ወረራ በፊት በነበሩት ፳ ዓመታት ውስጥ ከ፱ በላይ አዋጆች ወጥተው ነበር። ጀ ቫንደርሊንደን «የኢትዮጵያ ሕግ ምንጮች መግቢያ፤ ከ፲፫ኛው እስከ ፳ኛው መቶ ዓመት» *የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት*፣ ቅጽ ፫ ቁጥር ፩ (፲፱፻፶፱ ዓ/ም) ገጽ 202-03።

ለምሳሌ የ፲፱፻፳፫ ዓ/ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መርህን መሠረት አድርጎ የተደራጀና ብዙ የወንጀል ተግባራትን የሚሸፍን ነበር።[53]

በዚህ ወቅት የወጡ ሕጎች በሂደት የዘመናዊ ሕግ ይዘት አዳብረዋል። ለምሳሌ አዘውትረው *ሥራ* ላይ ለዋሉ ቃላትና ሐረጎች፣ እንዲሁም ጽንሰ-ሐሳቦች ትርጉም ተሰጥቷል። ሕግጋቱ በይዘታቸውና ሌሎች ምክንያቶች የተለያየ ደረጃ እንዲኖራቸው ስለተደረገ የተለያየ ስም እንዲኖራቸው ሆነ። ለምሳሌ አዋጅ፣ ድንጋጌ እና ትዕዛዝ ተብለው እንዲጠሩ ተደረገ።[54] ከዚህም ባለፈ ሕግ የማመንጨት *ሥ*ልጣን ለተለያዩ ተቋማት መስጠት የተጀመረ ሲሆን፣ ለምሳሌ ስለዳኝነት ጉዳዮች የፍርድ ሚኒስትሩ ሐሳባቸውን በጽሑፍ ለምክር ቤቶቹ እያቀረቡ እንዲያስጸድቁ ከሕገ መንግሥቱ ጋር አብሮ በወጣው ዝርዝር ሕግ ፱ኛው ምዕራፍ አንቀጽ ፷፯ እና ፷፰ *ሥ*ር ተደንግጓል።[55]

### ሸ) ቅድመ-ዘመናዊ የሕግ ትምህርት

ቀደም ብሎ እስከ ፲፱፻፳፫ ዓ/ም ድረስ የወንጀል ጉዳይን በተመለከተ ተፈጻሚ የነበረው ሕግ ፍትሐ ነገሥቱ ነበር። ፍትሐ ነገሥቱን የሚገልጡት የተለየ ችሎታ የነበራቸው የሕግ ሊቃውንት ሊቄ የተባለ ማዕረግ ይሰጣቸው እንደነበረ በተለያዩ ሰነዶች ላይ ተጠቅሷል።[56] የፍትሐ ነገሥት ትምህርት ከአብነት ትምህርት ጋር አብሮ የሚሰጥ በመሆኑ በመጀመሪያ ንባብ፣ ትርጓሜና የመሳሰሉትን ከተማሩ በኋላ የሚሰጥ ትምህርት ነበር። ለትምህርቱ በነበረው ከፍ ያለ ክብርና ተፈላጊነት ምክንያት ይመስላል ከሌሎቹ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎች የሚለየው በሠገነት መሰጠቱ ነው።[57] በዘመኑ ስለነበረው የሕግ ሳይንስ ቫንደርሊንደን በትንሹም ቢሆን ይጠቅሳል።[58]

## ፫ የሁለተኛው እርከን መሠረታዊ ለውጥ፣ ከ፲፱፻፴፬ እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም

ከዚህ በላይ የተመለከትነው ወቅት ተቋማትን ለመመሥረት የተደረገ ጅምር የታየበት ነበር። ከኢጣሊያ ወረራ በኋላ በእንግሊዞች የቴክኒክ ድጋፍ በፍትሕ አስተዳደር በኩል ብዙ መሠረት የሆኑ ተግባራት ተከናውነዋል። በዚህም መሠረት ሕግ ለሕዝብ የሚገለጥበት የመጀመሪያው መንግሥታዊ ጋዜጣ «ነጋሪት ጋዜጣ» ተብሎ ተቋቋመ። የዘመናዊ ዝርዝር ሕግጋት ክፍተት ስለነበረ ሕግ የሚያዘጋጅና የሚገመግም ኮሚቴ ተቋቋመ። በዚሁ ቡድን ትጋት ብዙ ዘመናዊ ሕግጋት ወጡ። እነዚህን ሕግጋት የሚተገብሩ ተቋማትም ተመሠረቱ። የእነርሱን *ሥ*ራ ጥራት ለመቆጣጠርም አስፈላጊ ተግባራት ተከወኑ። የወንጀል ፍትሕ አስተዳደሩ አሁን በምናውቀው መልኩ ተደራጀ።

---

[53] ይህ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በአማርኛ ብቻ የወጣ ሲሆን ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመው ከነፃነት በኋላ ነው። ቫንደርሊንደን፣ ገጽ 230፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁ 41።

[54] የ፲፱፻፳፫ ዓ/ም ሕገ-መንግሥት፣ አንቀጽ ፯፣ ፱።

[55] የዝርዝሩ መግለጫ (ማኅተመ ሥላሴ ከገጽ ፯፻፷፯ ጀምሮ)።

[56] Fitha Nagast: The Law of the Kings (trans. Abba Paulos Tzadwua 1968 G.C.) xx። ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ *የጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት* (አዲስ አበባ፣ 2013 ዓ/ም) ገጽ 317-23፣ 324።

[57] ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ ገጽ 324-26።

[58] ቫንደርሊንደን፣ ገጽ 220-25።

### *ሀ) የአስተዳደር መዋቅር እንደገና መደራጀት - የፍርድ ቤቶች አደረጃጀት*

ከአዋጁ ቅደም-ተከተል ቁጥር እንደምንረዳው ነጋሪት ጋዜጣ ከተቋቋመ በኋላ የወጣው አዋጅ ስለዳኝነት አካሄድ የሚደነግገው ነው።[59] ይህ አዋጅ ዘመናዊውን የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት አሁን በምናውቀው መልኩ ያቋቋመ ሲሆን ይህም በጊዜው የተከናወነውን መሠረታዊ የአስተዳደር አደረጃጀት ጥናት መሠረት ያደረገ ነበር። በዚሁ መሠረት በኢትዮጵያ አሥራ ሁለት አውራጃዎች ተዋቅረው፣ አውራጃዎቹ በወረዳና በቀበሌ ተከፍለዋል። ይህ የአገር ግዛት ደንብ (የአስተዳደር ደንብ) ስለዳኞች አሿሿምና አስተዳደር የሚደነግግ ሲሆን፣ የፍርድ ቤቱ አደረጃጀትም ይህንኑ የአስተደዳደር አደረጃጀት የተከተለ ነው።[60]

በአስተዳደር ደንቡ መሠረት ዳኞችና ሌሎች የመንግሥት ሹመኞች ከመንግሥት በሚከፈላቸው ደሞዝ እንደሚተዳደሩ፣ እንዲሁም አገረ ገዥዎቹ የየፍርድ ቤቶቻቸው ፕሬዚደንቶች መሆናቸውን ይደነግጋል። በመሆኑም ጠቅላይ አገረ ገዥው በሚቀመጥበት ከተማ በሚቋቋመው አውራጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እንደሚሆንና ሌሎቹ ሦስቱ ዳኞች በፍርድ ሚኒስትር አቅራቢነት በንጉሠ ነገሥቱ እንደሚሾሙ ይደነግጋል።[61] ጠቅላይ አገረ ገዥው ችሎት ማስቻል በማይችልበት ቀን የፍርድ ቤቱ ምክትል ፕሬዚዳንት በሰብሳቢነት እንደሚያስችል ደንቡ ይገልፃል።

በየወረዳው ለሚቋቋሙ ፍርድ ቤቶች ዋናው ዳኛ አገረ ገዥው ነው። ከእርሱ ጋር ሆነው የሚፈርዱ ሌሎች ከሁለት ያላነሱ ዳኞች እንደሚሾሙ፣ ስለይግባኙና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች በማዘዣ እንደሚደነገግ ተመልክቷል።[62] በየምስለኔዎቹ ግዛት ለሚቆሙ ፍርድ ቤቶችም ዋናው ዳኛ ምስለኔው ሲሆን ከሱ ጋር ሆነው የሚፈርዱ ዳኞችም በነገሠ ነገሥቱ እንደሚሾሙ ይደነግጋል።[63]

የፍርድ ቤቶችን አደረጃጀትና አሠራር በተመለከተ ስለዳኝነት አካሔድ የወጣው አዋጅ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣ አልነበረም። በዚሁ መሠረት ጠቅላይ የንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የአውራጃ ፍርድ ቤት እና የወረዳ ወይም የቀበሌ ፍርድ ቤት አቋቁሟል።[64] በሁሉም አውራጃዎች የአውራጃ ፍ/ቤቶች ተቋቁመው፣ እንደአስፈላጊነቱ የተለያየ ቁጥር ያላቸው ዳኞች እንደሚሾሙና ከመካከላቸው አንዱ የፍ/ቤቱ ፕሬዚዳንት እንደሚሆን ይደነግጋል። የአውራጃው ፍርድ ቤት በአውራጃው ግዛት በሙሉ ሥልጣን ያለው ሲሆን፣ ጉዳይ የሚታየው በሦስት ዳኞች ሆኖ ፍርድ የሚሰጠውም በአብላጫ ድምጽ ነው።

የአውራጃው ፍርድ ቤት የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ከዚህ ቀደም ከነበረው በተሻለ ግልጽ ሆኖ ተደንግጓል። በመሆኑም በእስራት እስከ አሥራ አምስት ዓመት የሚያስቀጣ፣ መቀጮን በተመለከተ እስከ ሁለት ሺህ ብር እንዲሁም ግርፋት እስከ ሃያ አምስት ጅራፍ ወይም በነዚህ ቅጣቶች በጣምራ የሚያስቀጣ ወንጀል የአውራጃው ፍርድ ቤት የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን እንደሆነ ይደነግጋል።

---

59 ስለዳኝነት ሥራ አካሄድ አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፵፬።

60 ያገር ግዛት ደንብ - ድንጋጌ ቁጥር ፩/፲፱፻፵፬። Nathan Marein, *The Ethiopian Empire - Federation and Laws* (Royale Netherlands Prining and Litograhing Company 1954) 27-28።

61 ያገር ግዛት ደንብ - ድንጋጌ ቁጥር ፩/፲፱፻፵፬፣ ክፍል ፸፰።

62 ዝኒ ከማሁ፣ ክፍል ፹፪።

63 ዝኒ ከማሁ፣ ክፍል ፹፫። ምስለኔ ከወረዳ ገዥ በታች ያለ የመንግሥት ሹመኛ ነው።

64 ስለዳኝነት ሥራ አካሄድ አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፵፬፣ አንቀጽ ፪።

የከፍተኛው ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ሲሆን የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ሥልጣን እንደሚኖረው በግልጽ ይደነግጋል። የከፍተኛው ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን በፍርድ ቤቱ በሚሠራበት ሕግ እንዲደነገግ የተተወ ሲሆን ከአውራጃው ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን በላይ የሆኑ ጉዳዮች በሙሉ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ሲታዩ ቆይተዋል። በፍትሐ ነገሥቱ እንደተደነገገው የሞት ፍርድ ለመፍረድ የሚችለው ንጉሡ ብቻ የነበረ ቢሆንም፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች የሞት ፍርድ የመፍረድ ሥልጣን ተሰጥቷል፤ ያም ሆኖ ግንን ቅጣቱ የሚፈጸመው በንጉሠ ነገሥቱ ሲጸና ነው።

በሌላ በኩል የንጉሠ ነገሥቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሥልጣን ብቻ እንዲኖረው ተደርጎ ተደንግጓል። የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት አፈ-ንጉሡ ሲሆን ከከፍተኛው ፍርድ ቤት የሚመጣን ይግባኝ በከፍተኛው ፕሬዚዳንት በሚመረጡና ጉዳዩን ባላዩት ሁለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር በመሆን ይግባኙን እንደሚመረምሩ ይደነግጋል። በዚህም ለረጅም ዘመናት በጠቅላይ ፍርድ ቤት የነበረውን የዳኛ እጥረት መረዳት ይገባል።

የወረዳው ፍርድ ቤት ወደፊት በትዕዛዝ እንደሚቋቋም የተደነገገ ቢሆንም ተከትሎ በተደረጉ ለውጦች አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም። ይህም የአስተዳደር ድንጋጌው በድንጋጌ ቁ ፯/፲፱፻፴፰ ሲሻሻል አውራጃ ጠቅላይ ግዛት ሆነ፣ ወረዳም አውራጃ ሆነ፣ ምስለኔ ደግሞ ወረዳ ግዛት ተብሎ ተለውጧል። ይህንኑ ተከትሎ የፍርድ ቤት አደረጃጀትም ተስተካክሏል።[65]

በዚህ አዋጅ ከተደረጉ መሠረታዊ ለውጦች አንዱ የይግባኝ መብት በአንድ መገደቡ ነው። ነገሩ በወረዳው ፍርድ ቤት ታይቶ ከሆነ ከወረዳ ፍርድ ቤት ወደ አውራጃ ፍርድ ቤት፣ በአውራጃው ፍርድ ቤት ታይቶ ከሆነ ከአውራጃ ፍርድ ቤት ወደ ከፍተኛው ፍርድ ቤት፣ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ታይቶ ከሆነ ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ወደ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ ይግባኝ ብቻ ይቻላል። የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቢፀና፣ ቢሻር፣ ወይም ቢሻሻል ድጋሚ ይግባኝ የለም። ሆኖም ይግባኝ የተባለበት ጉዳይ ለንጉሠ ነገሥት ችሎት ሊቀርብ ይችላል።

### ለ) የዳበሩ ሕግጋት መውጣትና የሌሎች ተቋማት ምሥረታ

ነጋሪት ጋዜጣ ኦፊሴላዊ ጋዜጣ ሆኖ ከተቋቋመ በኋላ ሕግጋቱ ቁጥራቸው ጨምሯል፤ ይዘታቸውና አደረጃጀታቸው በከፍተኛ ሁኔታ ዘመነ። ተቋማትን የሚያቋቁሙ ሕግጋት፣ ተቋማቱ የሚሠሩባቸው ፍሬ እና የሥነሥርዓት ሕግጋት ወጥተዋል። ለዚሁ የሕግ አወጣጥ መዘመን የሚመጥን የሕግ አወጣጥ ሥርዓትም ተዘረጋ።

ለሕግጋቱ መዳበር ዋና ምክንያት ከሆኑት ምክንያቶች መካከል አንዱ የሕግ አዘጋጅና ገምጋሚ ኮሚቴ መቋቋም ነው።[66] በዚህ ድንጋጌ መሠረት የኮሚቴው አባላት የሆኑት የንጉሠ ነገሥቱ የሕግ አማካሪ፣ የከፍተኛው ፍ/ቤት ፕሬዚደንት፣ በሕግ የተመረቁ ሦስት ባለሙያዎች፣ በፍርድ ሥራ የረጅም ጊዜ ልምድ ያላቸው፣ ወይም ሕግን አጥርተው የሚያውቁ ሰዎች ናቸው። በተለያየ ጊዜ የአባላቱ ቁጥር የተለዋወጠ ሲሆን፣[67] በ፲፱፻፵፬

[65] ያገር አገዛዝ ደንብ ማሻሻያ - ድንጋጌ ቁጥር ፯/፲፱፻፴፰። በዚህ ዘመን የአገሪቱ አስተዳደር በተዋረድ 12 ጠቅላይ ግዛት፣ 70 አውራጃዎች፣ 338 ወረዳዎችና 976 ምክትል ወረዳዎች የተከፋፈለ ነበር።

[66] ስለዳኝነት ሥራ አካሄድ አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፴፬፣ አንቀጽ ፳፩።

[67] ለምሳሌ ብላታ ቅጣው መጋቢት 16 ቀን 1946 ዓ/ም «ሕግ አዘጋጅ ጉባዔ» ተመሥርቶ የዋናዋናዎቹ ኮዶች ዝግጅትን በበላይነት ሲመራና ሲቆጣጠር እንደነበር ይጠቅሳሉ። ብላታ ቅጣው ይታጠቁ፣

ዓ/ም በሕግ መርማሪ ጉባዔው በተዘጋጀው ረቂቅ ሕግጋት ሪፖርት ውስጥ እንደተመለከተው በጉባዔው አባልነት ስማቸው የተጠቀሰው የሚከተሉት ናቸው፡-[68]

- ክቡር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ፣ የፍርድ ሚኒስትር ሊቀመንበር
- ክቡር አፈንጉሥ ታደሰ መንገሻ አባል
- ዶ/ር ዊሊያም ቦያጃር፣ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አባል
- ሰር ቻርለስ ማቲው፣ የሕግ አማካሪ አባል
- ሚስተር ናታን ማሬን፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አባል
- ሊቀ መጠኑ ወረደቃል ወንድም፣ በግርማዊ ን/ነ ካቢኔ ሕግ ክፍል አባል
- ሚስተር ግራሾ ወለኪ፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኛ አባል
- አቶ በረከተአብ ሃብተሥላሴ አባል
- አቶ በላቸው አሥራት አባል
- አቶ ንርአዮ ኢሳያስ አባል
- አቶ መሐመድ አብዱራህማን አባል

ይህ አማካሪ ጉባዔ የሕግ ረቂቅ ዝግጅትና ግምገማ ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ ግንዛቤ እንዲወስድበት የተጣለበት ገደብ የሚያዘጋጀው ረቂቅ ሕግ «የተፈጥሮን ፍትሕና የሰውን ሕሊና የማይቃወም፤ በኢትዮጵያና በውጭ አገር ሰዎች መካከልም ልዩነት ሳይኖረው እንዲጸናባቸው የሚገባና የሚስማማ ነው ብሎ ኮሚቴው፤ ሲሆን ባንድ ቃል አለዚያም አብዛኙ ወገን መስክሮ በፊርማው» የሚያረጋግጠው መሆን እንዳለበት ይደነግጋል።[69] ይህም ገደብ ወደፊት ስለሚወጡት ሕግጋት ብቻ ሳይሆን በጊዜው ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕግጋት ሲደነገግ «እስካሁን ከሚሠራባቸው ሕጎች ውስጥ ለሰውነት ሕሊናና ለተፈጥሮ ፍትሕ ተቃዋሚ የሆኑት፤ ወይም በኛ ዜጎችና በውጭ አገር ሰዎች መካከል የማይገባ ልዩነት የሚያደርጉት ሕጎች …ማንኛውም ፍርድ ቤት እንዳይሠራባቸው በዚህ አዋጅ ተከልክሏል» በማለት ይደነግጋል።

ሕግ የሚወጣላቸው ተግባራት ብዛት ያላቸውና ሌሎች ነገሮች ግንዛቤ መደረግ ያለባቸው በመሆኑ በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ለሌሎች የመንግሥት ተቋማትና ሹመኞች በውክልና ሕግ ማውጣት በሰፊው ቀጠለ። በዚህም መሠረት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሚሠራበትን የሥነ-ሥርዓት ሕግ እንደቀደም ተከተላቸው በአፈ-ንጉሡ እና በከፍተኛው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አዘጋጅተው በመመሪያ መልክ እንዲያወጡ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል።[70]

---

ስለዳኝነት (ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ፲፱፻፶፬ ዓ/ም) መቅድም። ማሬን ግን የተለያዩ ሰዎች በተለያየ ጊዜ ስለመሾማቸው ይጠቅሳል። Marein፣ 29-30።

68 ከሕግ መርማሪ ጉባዔ ለሚንስትሮች ም/ቤት የቀረበ የሕግ ረቂቅ ሪፖርት ቁ ፩፻፸፯ (መስከረም ፱ ቀን ፲፱፻፶፬ ዓ/ም)። በዚህ ሪፖርት ውስጥ አምስት ረቂቅ ሕግጋት የተጠቃለሉበት ሲሆን የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ፣ ስለፌደራል ዳኝነት ሥልጣን በኤርትራ እና የዳኝንት ሥራ አካሄድን ማሻሻያ ይጨምራል።

69 ስለዳኝነት ሥራ አካሄድ አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፴፬፣ አንቀጽ ፳፩።

70 ለምሳሌ አፈ-ንጉሡ (የፍርድ ሚኒስትሩ) የንጉሠ ነገሥቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ስለሚሰማበት ሥነ-ሥርዓት እንዲያወጣ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ስለጠቅላይ የንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥነ-ሥርዓት ፲፱፻፴፫ ዓ/ም የወጣ ደንብ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር ፩፻፶፫/፲፱፻፴፫ ዓ/ም አወጣ። እንደዚሁም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት የከፍተኛው እና የአውራጃ ፍርድ ቤቶች ስለሚሠሩበት የሥነ-ሥርዓት ሕግ እንዲያወጣ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ስለፍርድ ቤቶች ሥርዓት አፈጻጸም በ፲፱፻፴፭ ዓ/ም የወጣ ደንብ፣ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር ፸፩/፲፱፻፴፭ ዓ/ም አወጣ። እነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች የፍትሕ ሥነ-ሥርዓት ሂደቱን በወቅቱ መልክ ያስያዙት ብቻ ሳይሆን አሁን ላሉትም የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች መሠረት ያስቀመጡ ናቸው።

ሕግጋቱ በይዘታቸውና ሌሎች ምክንያቶች የተለያየ ደረጃ እንዲኖራቸው ስለተደረገ፣ በተለያየ ጊዜና በተለያየ ደረጃ እንዲወጡ እንዲሁም ሕግጋቱ የተለያዩ መሆን እንዳለባቸው አስገደደ። በዚህም ምክንያት አዋጅ፣ ደንብ፣ ትዕዛዝ፣ ድንጋጌ እና የሕግ ክፍል ማስታወቂያ እየተባሉ ይጠቀሱ ነበር።[71]

ከዚህ በላይ ከተመለከተው የፍርድ ቤት መቋቋምና አወቃቀር በተጨማሪ በዘመናዊ የፍትሕ ሥርዓት ሌሎች ተቋማት ለምሳሌ የዓቃቤ ሕግና ፖሊስ መኖር አስፈላጊ ነው። አሁን በምናውቀው መልኩ የተቋቋሙትን እነዚህን የፍትሕ ተቋማት ከዚህ በታች በአጭሩ እንመለከታለን።

*ስለዐቃቤ ሕግ ሥራ*

*ስለ ዓቃብያነ ሕግ የወጣ ያ፲፱፻፴፬ ዓ/ም አዋጅ* በደነገገው መሠረት ዐቃቤ ሕግ ተቋቋመ። ከዚህ በፊት «ሕግ አስከባሪ» ተብሎ ይታወቅ የነበረው ተቋም ለመጀመሪያ ጊዜ «ዐቃቤ ሕግ» የሚለው መጠሪያ ተሰጠው። ትርጉሙም «በፍርድ ቤቶች ዘንድ ለሚቀርበው ክርክር ሕግን የሚያስከብር ጠበቃ ነው፤ ሥራውም በጠቅላላው የሕዝብን ጸጥታ የሚነኩትን ሕጎች እንዲከበሩ ማድረግ ነው» ይላል።[72] ሥልጣኑ በወንጀል ጉዳይ የማንንም ፈቃድ ሳይጠይቅ ፍርድ ቤት ቀርቦ መከራከር ሲሆን ይህም ምርመራንና ይግባኝን ጨምሮ ማንኛውንም ሙግት ያጠቃልላል።[73] በፍርድ ሚኒስትሩ የሚመራ ሆኖ በከፍተኛ ፍርድ ቤትና በአውራጃው ፍርድ ቤቶች ከሳሽ ከሚያመለክታቸው ትንንሽ ነገሮች ሌላ ማናቸውንም ክስ ዐቃቤ ሕጉ ማመልከት እንዳለበት ይደነግጋል።[74]

በዚህ አዋጅ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለፁት የሕግ መርሆዎች (1) ዐቃቤ ሕግ በራሱ ሥልጣን ክስ መመሥረት እንደሚችል፣ (2) በፍርድ ቤት ፈቃድ ወይም በዋናው ዐቃቤ ሕግ ትዕዛዝ ክስ ማቋረጥ እንደሚችል፣ (3) ዐቃቤ ሕግ ክሱን በማቋረጡ ምክንያት ወይም በመንግሥት ትዕዛዝ ተከሳሹ መከላከያ ማስረጃውን ሳያሰማ የተለቀቀ እንደሆነ ለጊዜው እንደሚለቀቅና ድጋሚ ለመክሰስ እንደማይከለክል፣[75] መከላከያ ማስረጃውን አሰምቶ ከሆነ ግን ተከሳሽ በነፃ እንደሚለቀቅና ሁለተኛ እንደማይከሰስ፣[76] (4) ሆኖም ትንንሽ በተባሉ ጉዳዮች ላይ በግል ከሳሾች ጉዳዩ በዐቃቤ ሕጉ በሚሰጥ መመሪያ መሠረት ሊቀጥል እንደሚችል ይደነግጋል።[77] በመጨረሻም አዋጁ ተሻሽሎ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ/ም አንድ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ እና ምክትል ጠቀላይ ዐቃቤ ሕግ ሊሾም እንደሚችል ተደነገገ።[78]

*የፖሊስ ተግባር*

ፖሊስ በዘመናዊ መልኩ የተቋቋመው በ፲፱፻፴፬ የፖሊስ አዋጅ (ቁጥር ፮) መሠረት ነው። ተግባሩም «ወንጀል እንዳይሠራ መከላከል፣ መፈተሽና በደለኛውን ወደ ፍርድ ቤት ማቅረብ፣ ሰላምና መልካም አስተዳደርን ማጽናት፣ ጥፋተኞችን መያዝ፣ ሰዎችንና ገንዘባቸውን መጠበቅ፣ በመንገድ ላይም የሚተላለፈው ሁሉ ደንቡን አክብሮ እንዲኖር

[71] የሕጉ ተዋረድ ልዩነት እንዳለው የተመለከተው በ፲፱፻፳፫ ዓ/ም ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፯ እና ፱።
[72] ስለ ዓቃብያነ ሕግ የወጣ ያ፲፱፻፴፬ ዓ/ም አዋጅ፣ አንቀጽ ፪።
[73] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፯።
[74] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፭ እና ፮።
[75] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፰(ሀ) እና ፲።
[76] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፰(ለ)
[77] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፮ እና ፯።
[78] የዓቃብያነ ሕግ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፰/፲፱፻፵፫።

*መቆጣጠር»* እንዲሁም የሚሰጠውን *ትዕዛዝ መፈጸም* ነው::[79] ከዚህም ባለፈ አዋጁ አንድ ፖሊስ ባልደረባ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት እንዲሁም በተወሰኑ ጉዳዮች ያለፍርድ ቤት ፈቃድ ሰውን ለመያዝ፣[80] ብርበራ ማከናወን[81] ሥልጣን ተሰጥቶታል::

*ስለ ወህኒ ቤት*

የእሥር ቅጣት በመደበኛው ዜጋ ላይ ተፈጻሚ የማይሆነው ለዘወትር ማቆያ የሚሆን ማረፊያ ቦታ ባለመኖሩ ነበር:: ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በ፲፱፻፲፯ ዓ/ም የመሠረቱት ወህኒ ቤት ጠባብና ጤንነቱ ያልተጠበቀ በመሆኑ ቀ/ኃ/ሥ በ፲፱፻፳፫ ዓ/ም ሌላ ወህኒ ቤት ገንብተው ቋሚ ጠባቂ እንደተቀጠረለት ጠቅሰዋል::[82] ይህ ወህኒ ቤት ነው በ፲፱፻፵፯ ዓ/ም *የወህኒ ቤቶች አዋጅ* ሲመሠረት የመጀመሪያው ወህኒ ቤት ሆኖ አገልግሎቱን የቀጠለው:: በዚህ አዋጅ ለመጀመሪያ ጊዜ ዐበይት መርሆዎች ተካተዋል:: (1) ማንኛውም የተፈረደበትም ሆነ በማረፊያ ቤት ሆኖ ጉዳዩን የሚከታተል ያልተፈረደበት ሰው ያለእስር ትዕዛዝ ሊታሰር እንደማይችል አዋጁ ይደነግጋል፤[83] (2) እሥር የተፈረደበት ሰው በወህኒ ግቢ ወይም ከግቢ ውጭ የሚሰጠውን ሥራ የመሥራት ግዴታ እንዳበት ተደንግጓል::[84] (3) ከሁለት ወር በላይ እና ከሦስት ዓመት በታች እሥራት የተፈረደበት ሰው የሁለት ወር እሥራቱን ከፈጸመ በኋላ መልካም ጠባይ ያሳየ እንደሆነ የቅጣቱን አንድ ሦስተኛ ሳይጨርስ ሊለቀቅ እንደሚችል ይደነግጋል:: እስከ ዕድሜ ልክ እሥራት የተፈረደበት ሰው 15 ዓመት ከጨረሰ በኋላ ሊፈታ እንደሚችል ይደነግጋል::[85]

**ሐ) ልዩ የጦር ፍርድ ቤት**

በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ በኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ላይ ከፍተኛ በደል ተፈጽሟል:: ያም ሆኖ ግን፣ ይህን መሠረት ያደረገ በጀርመን ወይም በጃፓን የተመሠረተው ዓይነት ልዩ ፍርድ ቤት በኢትዮጵያ አልተረመሠረተም:: በመሆኑም ኢትዮጵያ የራሷን ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር ፹፯/፲፱፻፵፱ መሥርታ ጉዳዩ በዚሁ ፍ/ቤት እንዲታይ ተደርጓል::[86] ፍርድ ቤቱ በ፲፱፻፳፫ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የመጀመሪያው ምዕራፍ በ፩ኛው ክፍልና በሦስተኛው ምዕራፍ በ፪ኛው ክፍል[87] የተመለከቱትን ወንጀሎች ብቻ ለማየት ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን፣ ካሉት ውስን መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው ጉዳያቸው የታየው ጥቂት ኢትዮጵያዊያን ብቻ ናቸው:: በዚህ ፍርድ ቤት የሚሰየሙት ዳኞች ዘጠኝ ሲሆኑ እነሱም (1) አራት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኞች፣ (2) ሦስት ከሌተና ኮሎኔል ማዕረግ በታች ያልሆኑ የጦር ሹሞች፣ (3) ሁለት ከአገረ ገዥ በታች ያልሆኑ የሲቪል መንግሥት ሹማምንት ናቸው:: ችሎቱም ከእነዚህ ዳኞች ውስጥ ሰባቱ ከተገኙ ተሟልቶ ይሰየም ነበር::

---

[79] የ፲፱፻፵፬ የፖሊስ አዋጅ፣ አንቀጽ ፳፩፣ ፲፫(፫)::
[80] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፲፫(፫)፣ እና ፲፬::
[81] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፲፩::
[82] ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ገጽ ፺፪::
[83] የ፲፱፻፵፯ ዓ/ም የወህኒ ቤቶች አዋጅ፣ አንቀጽ ፯::
[84] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፰::
[85] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፱(፩)፣ (፬)::
[86] የንጉሠ ነገሥቱን ግዛት ጸጥታ ስለሚነኩ አንዳንድ ወንጀለኞች የዳኝነት ሥራ አካሄድ የወጣ አዋጅ (ቁጥር፹፯/፲፱፻፵፱ ዓ/ም)::
[87] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፱:: የወንጀል ሕጉ የመጀመሪያው ክፍል የመንግሥትን ደህንነተ የተመለከተው ነው:: ሰዎቹም የተከሰሱት በአገር ክደት ወንጀል ነበር::

ክሱ የሚዘጋጀው በፍርድ ሚኒስትሩ ሲሆን ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ጋር በመመካከር ነው። ፍርድ ቤቱ የራሱን የአሠራር ሥነ-ሥርዓት ደንብ እንዲከተልም ተደንግጓል። ለሥራው አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን ትዕዛዛት ለመስጠት ሥልጣን ተሰጥቶታል። ፍርድም የሚሰጠው በአብላጫ ድምጽ ነው። በወንጀል ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩ የጦር ፍርድ ቤት የሚወስነው ቅጣት ሀብት መውረስና ከማዕረግ መሻርን ይጨምራል።[88] በችሎቱ ፍርድ ይግባኝ የሚቀርበው ለሌሎች አምስት ዳኞች ሲሆን እነሱም በያዙት ሥልጣን ምክንያት የሚሾሙ ናቸው። በዚሁ መሠረት የንጉሠ ነገሥቱ አፈንጉሥ ሰብሳቢ ሆኖ የሕግ መወሰኛውና የሕግ መምሪያው ፕሬዚደንቶች፣ ከዘውድ አማካሪ አንድ እና አንድ ሌላ ከፍተኛ የጦር ጄነራል ይሰየማሉ።

በዚህ ችሎት ጉዳያቸው ከታየ ተከሳሾች መካከል አንዱ ደጃች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ሲሆኑ እርሳቸውም የቀ/ኃ/ሥ አማች ነበሩ። የትግራይ አገረ ገዥ ሳሉ በኢጣሊያ ወረራ ወቅት የአካባቢውን ጦር እንዲመሩ ተደርገው የኢትዮጵያ ሠራዊት እንዲሸነፍና ኢጣሊያ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ዘልቆ እንዲገባ አድርገዋል። በኋላም ለዚህ ውለታቸውና ለኢጣሊያ በማደራቸው ኢጣሊያ የፈለጉትን ሹመት ሰጥቶ የትግራይ ገዥ አደረጋቸው። ጉዳያቸው ታይቶ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው ቢሆንም፣ ይቅርታ ጠይቀው ቅጣቱ ወደ እድሜ ልክ እሥራት ተቀየረ። ደርግ ወደ ሥልጣን ሲመጣ ከእሥር ከተፈቱ በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

ሁለተኛው ሰው በሮም የኢትዮጵያ ጉዳይ አስፈጻሚ የነበሩት ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ሲሆኑ ለኢጣሊያ በማደር አገልግለው የአፈ-ቄሳርነት ማዕረግ በኢጣሊያ መንግሥት ተሰጥቷቸው ነበር። ከነፃነት በኋላ በዚሁ ችሎት «በአገር ክህደት ወንጀል ለፍርድ ቀርበው የሞት ፍርድ» የተፈረደባቸው ቢሆንም፣ ፍርዱ «ወደ እድሜ ልክ እሥራት ተቀይሮ ወደ ጅማ ተጋዙ»።[89]

### መ) የፌደራል ፍርድ ቤት

በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ መሠረት ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ በፌደሬሽን ስትዋሃድ፣ አዲሱን ክስተት ለማስተናገድ ሲባል ሦስት ዋና ዋና ሕግጋት ወጥተዋል። እነሱም የኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር መዋሃድ የሚያውጀው ድንጋጌ፣ ስለሕዝብ መብት የወጣው አዋጅ፣[90] እና የፌደራል ወንጀል ሕግን[91] የሚያጠቃልል ነው። ይህንንም ለመዳኘት እንዲያስችል የፌደራል ዳኝነት ተደንግጓል።[92] ይህም የፌደራል ዳኝነት ሥልጣን ለአውራጃ፣ ለወረዳዎች እና ቀበሌዎች በአዋጅ ቁ ፪/፲፱፻፴፬ ዓ/ም በተደነገገው ላይ ተጨማሪ ሆኖ የተሰጠ ነው። ሆኖም የራሱ ፕሬዚደንት ያለው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቋቁማል።[93]

---

88 የንጉሠ ነገሥቱን ግዛት ጸጥታ ስለሚነኩ አንዳንድ ወንጀለኞች የዳኞነት ሥራ አካሄድ የወጣ አዋጅ (ቁጥር፹፯/፲፱፻፴፱ ዓ/ም) አንቀጽ ፮።

89 ባሕሩ ዘውዴ፣ ገጽ 78-85።

90 ስለሕዝበዊ መብት የወጣ አዋጅ (ቁጥር ፩፻፴፱/፲፱፻፵፬)። የሕዝባዊ መብት አዋጅ የወጣው ሕገ-መንግሥቱ ተሻሽሎ የዜጎችን መብት በተሻለ የሚያስከብር እስከሚሆን ድረስ የመብት ድንጋጌ የተጠቃለለበት ሲሆን፣ የፌደራል ወንጀሉ ደግሞ ፌደሬሽኑን ለመጠበቅ የወጣ ነበር። ማሬን እነዚህ ሕግጋት አዲሱን ክስትተ ለመስተናገድ በጥድፊያ የወጡ ናቸው ይላል። Marein፣ ገጽ 22-23.

91 የፌደራል ወንጀሎች አዋጅ (ቁጥር ፩፻፴፰/፲፱፻፵፬)።

92 የኢትዮጵያ ፌደራል የዳኝነት ሥልጣን አዋጅ (ቁጥር ፩፻፴/፲፱፻፵፭)።

93 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፪ የመጀመሪያውና ሁለተኛው አነጋገር።

የወንጀል የዳኝነት ሥልጣንን በተመለከተ በፌደራል ወንጀል አዋጅ የተደነገጉትንና ወንጀል ስለመሆናቸው ከዚህ በፊት በወጡ ሕግጋት የተደነገጉትን በመተላለፍ (፩) በፌደራሉ ንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ (፪) በፌደራሉ መንግሥት፣ በፌደራሉ ሹም፣ ሠራተኛ ወይም የፌደራሉን ሥራ በሚሠራ ሰው ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ (፫) የፌደራሉን ሥራ ወይም አሠራር ለማሰናከል በፌደራሉ ሹም ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ (፬) በንጉሠ ነገሥቱ መከላከያ ወይም ብሔራዊ ጸጥታ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ (፭) ዜጎች በሕግ የተሰጣቸውን መብት እንዳይገለገሉበት በማድረግ የሚፈጸሙ ወንጀሎች[94] በየፌደራል ዳኝነት ሥልጣን ሥር ተካተቱ።

የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአካል ተለይቶ የተቋቋመ ሳይሆን የከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን እንዲኖረው ሆኖ የተሰየመ ነበር። ከሦስቱ ዳኞች አንዱ ኤርትራዊ እንዲሆን አዋጁ ያስገድዳል። የንጉሠ ነገሥቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የፌደራል ዳኝነት ሥልጣን ተግባሩን ሲያከናውን አፈ ንጉሡ ፕሬዚደንት ሆኖ የሚያስችልበት አንዱ ኤርትራዊ የሆነ ሁለት ዳኞች ጋር ያስችላል። ይግባኙም የሚሰማው የከፍተኛው ፍ/ቤት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆኖ በሰጠው ፍርድ ላይ ነው።[95]

## ፬ ስለሕግ አረዳዳችን አንዳንድ ምልከታዎች

በኢትዮጵያ ሕግጋት ውስጥ ያሉትን እሳቤዎችና ድንጋጌዎች፣ እንዲሁም የነገሥታቱንና የዳኞችን የዳኝነት አሠራር ስንመረምር የሕግ አረዳዳችን በምዕራቡ ዓለም እንደታየው ሁሉ በየጊዜው እየተለወጠ የመጣ መሆኑን እንገነዘባን። ለምሳሌ ቀደም ባለው ዘመን ሕግጋቱ በሙሉ ከሃይማኖታዊ ቀኖና ጋር በእጅጉ የተቆራኙ በመሆኑና ወንጀልም ኃጢአት ተደርጎ ይታይ ስለነበረ፣ ንጉሡም በምድር የእግዚአብሔር ወኪል ተደርጎ ዳኝነትና ፍትሕ ይሰጣል ተብሎ ይታመን ስለነበረ የተፈጥሮአዊ ወይም መለኮታዊ የሕግ አረዳድ እንደነበረን ግልጽ ነው። በዚህም ዘመን ቢሆን ሕግን ለመተግበር የተደረገው ጥረት አስገራሚ መሆኑን ከተወሰኑት ጥቂት ምሳሌዎች ግንዛቤ መውሰድ ይቻላል። ለምሳሌ ሱራሄ ክርስቶስ የተባለው የወልቃይት ገዥ በንጉሡ ላይ አምጾ በጎንደሩ እጨጌ ጥገኝነት ሲጠይቅ ንጉሡ እጁን ስጡኝ ብለው አልተከራከሩም። ደብረ ሊባኖስ ለነበሩት ሊቃውንት መልዕክት ልከው ይህን ሰው ከሞት የሚያተርፈው ሕግ ካለ መርምሩ ብለው ነበር የጠየቁት። ይህ ምሳሌም ሆነ አገላለጹ ግርድፍ በመሆኑ ብዙ ጥያቄዎች ሊነሱ እንደሚችሉ ግልጽ ነው።

የመጀመሪያዎቹ ሚኒስቴሮች ሲመሠረቱ የነርሱ ማቋቋሚያና የሚሠሩበት ደንብ በንጉሠ ነገሥቱ የተሰጠ ነበር። በሂደትም በሕግ የሚገዙት ጉዳዮች እየተበራከቱና መንግሥትም በሕግ ለመግዛት የሚፈልገው ተግባር እየሰፋ በመሄዱ ሕግጋቱ እየበዙ፣ ይዘታቸውና አደረጃጀታቸውም እየዘመነ መጣ። የመጀመሪያው ሕገ መንግሥት ዳኞች «በሕጉ የተጻፉትን ቃሎች እየጠበቁ» እንደሚፈርዱ ደንግጓል።[96] ለዚህም ተመራጭ የሆነበት ምክንያት የሕጉ ግልጽነት ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ የመጀመሪያውን ሕገ መንግሥት በፈረሙ ጊዜ ስለ ሕጉ ግርማ ሲገልጹ «መከበርም መጠቀምም የሚገኙት ከሕግ መተካከል የተነሣ ነው፤ መዋረድም መጎዳትም የሚመጡት ከሕግ መጓደል የተነሣ ነው፤ ግፍም በደልም የሚበዙት ሕግ ባለመቆሙ

---

94 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፪(ረ) ከ(፩) እስከ (፬)፣ ፪(ሰ)።
95 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፫ እና ፬።
96 ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ ፶።

ነው» ብለዋል፡፡[97] ይህንንም መሠረት በማድረግ ስለ ሕጉ ሰባት ያህል መርሆዎች ተጠቅሰዋል፤ የመጀመሪያዎቹ ሁለት መርሆዎች የዜጎች ግላዊ መብትና የጠቅላላው ጥቅም መመጣጠንና የሕግ ጠቃሚነቱም ሆነ ቀጪነቱ ለሁሉም እኩል ተፈጻሚ መሆን እንደሚገባቸው የሚገልፁ ናቸው፡፡

ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት የሕገ መንግሥቱንና የሕጉን ይዘት ሲያብራሩ ሕግ በአንድ በኩል የመንግሥት ሥልጣን መግሪያ ሲሆን በሌላ በኩል በመንግሥት የሚጣል ግዴታና የማይደፈር ጽኑ ኃይል መሆኑን ገልጸዋል፡፡[98] በተለይም በዓመቱ ባደረጉት ንግግር ከሥልጣን ሕጋዊነትና ከሉዓላዊነት ጋር በማሰባጠር ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት፣ ኃይል ሕግን እንደሚያጸና፣ ሥልጣንም ተቀባይነት የሚኖረው በሕግ እንደሆነ የሕግን መሣሪያነት ተንትነዋል፡፡ ሕግና የጦር ሠራዊት ንጉሥና ሕዝቡን ያስከብራሉ፣ ምክንያቱም የንጉሡን ሥልጣንና የሕዝብን ጥቅም መቃወም ያስቀጣል በማለት አብራርተዋል፡፡[99] ተክለ ሐዋርያት ሕግ ለዜጎች ነፃነትን እንደሚያጎናፅፍ ያብራሩ ሲሆን ነፃነት ማለት ግን መረንነት ባለመሆኑ፣ ይህንንም ለማስከበር የንጉሡ ነገሥቱ መንግሥት ኃይል በጣም የበቃ እንደሆነ ለመኳንንቱ አስረድተዋል፡፡

ይህ ዘመን ዜጎች የሚተዳደሩበት ሕግ ከመለኮታዊው ሕግ ይልቅ ንጉሡ (በኋላም ምክር ቤቱ) የሚደነግጉት ሕግ እየበዛ በመምጣቱ ተደንጋጊነት (positivism) ሥር እየሰደደ የመጣ ቢመስልም ይህ ሕግ «የተፈጥሮን ፍትሕና የሰውን ሕሊና የማይቃወም» መሆን እንዳለበትና ይህንን መጠይቅ የማያሟላ ሕግ የማይጸና ስለመሆኑ በንጉሠ ነገሥቱ ተደንግጓል፡፡[100]

በብዙ ቀደምት ጽሑፎች ስለ ሕዝቡ ፍትሕ መሻትና የአደባባይ ውሎ ብንመለከትም፣ የፍትሕ አስተዳደር በደል አልነበረም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ ከበደ እንግዳሰው (የሕግ መወሰኛው ምክር ቤት ቃለ ጉባዔ ጸሐፊ የነበሩት ፲፱፻፶ ዓ/ም) ዋና ዋናዎቹ ሕግጋት ከወጡ በኋላ የሕጉን ግልጽነት፣ የሕዝቡን የፍትሕ ጥማትና የዳኞችን ግዴታ አመልክተዋል፡፡ በጊዜው የነበረውን የፍትሕ ችግር ሲጠቅሱ ንጉሠ ነገሥቱ በችሎት ፍርድ ማቃናታቸውን ጠቅሰው፣ የአዳዲሶቹ መድብለ ሕጎች (Codes) መውጣት ብዙ ችግር እንደሚቀርፍ አመልክተዋል፡፡ በመጀመሪያ ሰው ሁሉ ሕጉን እያነበበ የሚያዋጣውንና የማያዋጣውን ጉዳይ ስለሚለይ የፍርድ ቤት ሙግት እንደሚቀንስ ተንብየዋል፤ የወንጀልም ጉዳይ ቢሆን ሕዝቡ ከወንጀል ተግባር አጥብቆ ይርቃል ብለዋል፡፡ የዳኝነት ሥራውን በተመለከተ ከበደ እንግዳሰው የሚከተለውን ገልፀዋል፡-

> ከዚህ በፊት በፍርድ ቤትም ሆነ በተሰጣቸው የፍርድ ሥራ ላይ የሚገኙ ዳኞች ጥሩ ስም ያላቸው ጥቂቶች ናቸው፡፡ … አሁን ግን ሕግና ዳኞች ከሳሽና ተከሳሽን የሚለያይ፣ ለአገሌ የማይል፣ የእውነት መብትን አጥብቆ ያዘለ፣ የፍትሐ ብሔር ሕግ … የወንጀለኛ መቅጫ ድንጋጌዎችና ሕጎች እንደመስታወት ጥርት … ቁልጭ ብለው ተሠርተዋል፡፡ ስለዚህ ወደፊት ዳኞችና ሐሜተኞች የእርቅ ውላቸውን በሚገባ ፈጽመዋል፤ … ከእንግዲህ ወዲያ ለሚደረገው የፍርድ ጉድለት ፈራጅን እንጂ አስፈራጅን አለመሆኑን [ያውቁታል]፡፡ …

---

[97] ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ገጽ ፯፻፷፬፡፡

[98] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ ፷፻፫፣ ፷፻፮፣ ፷፻፯፡፡

[99] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ ከ፷፻፲፬ እስከ ፷፻፲፱፡፡

[100] ስለዳኝነት ሥራ አካሄድ አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፵፬፣ አንቀጽ ፳፩፡፡

ብለዋል::[101] ሆኖም የእነዚህን ሕግጋት መጽደቅ ተከትሎ በኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት ይታተሙ የነበሩትን ጽሑፎችና ፍርዶች ለመረመረ ሰው የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ግልጽ እንዳልነበረ፣ የጠቅላላውን ክፍል ድንጋጌዎች ከልዩ ክፍል ድንጋጌዎች ጋር እያሰባጠሩና እያቀናጁ መረዳትም ቀላል እንዳልነበረ (አሁንም እንዳልሆነ) ግልጽ ነው::

## ፰ ማጠቃለያ

ዳግማዊ ምኒልክ ዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር ካቋቋሙበት ዘመን ጀምሮ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ብዙ ለውጦች አሳይቷል:: ከ፲፱፻ ጀምሮ እስከ ፲፱፻፳፯ ዓ/ም ያለው ለውጥ የተቋማት ግንባታ ላይ ያተኮረ መሆኑን በሁለት እርከኖች ከፍለን ተመልክተናል:: የመጀመሪያው ዘመን ከ፲፱፻ ጀምሮ እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ድረስ ያለው ሲሆን የወንጀል ችሎቱ ለብቻው እንዲቆም መደረጉ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መውጣት፣ የክርክር አሰማምና የይግባኝ ሂደት አመራር የተመለከቱ ድንጋጌዎች መውጣታቸው በዚህ ዘመን የተከናወኑ ተግባራት ናቸው::

ከኢጣሊያ ወረራ ማብቂያ በኋላ ያለው ዘመን የእንግሊዝ የቴክኒክ ድጋፍ የተጨመረበት ስለነበረ፣ ነጋሪት ጋዜጣ የሕግ የኦፊሴል ጋዜጣ ሆኖ እንዲቋቋም ተደርጓል:: ይህንኑ ተከትሎም በቀጣዮቹ አሠርታት (decades)) ብዙ ፍሬ ሕግ እና የሥነ-ሥርዓት ሕግጋት በተሻለ መልኩ ወጥተዋል:: የሕግ አወጣጡ ሥርዓትና ሕግጋቱ የዘመኑ ሲሆን፣ በአንድ ቀን በምክር ቤቱ ብዙ ሕግጋት ይጸድቁ ነበር:: በዚህ ዘመን ሌሎች የፍትሕ ተቋማት፣ ለምሳሌ ዐቃቤ ሕግ፣ ፖሊስ እና ማረሚያ ቤት የተመሠረቱ ከመሆናቸው ባሻገር የጥብቅና ተቋምም እውቅና ተሰጥቶታል::

ይህ ዘመን ብዙ መርሆዎች በሕጎች የተካተቱበትና የተቋማቱ ዘመናዊ አሠራር የታየበት ነው:: ለምሳሌ የፍርድ ቤት ትዕዛዝን መሠረት ያደረገ እሥራት፣ የእሥራት ቅጣትን ዋና ቅጣት ማድረግ፣ በአመክሮ መፈታት ወዘተ በዚህ ዘመን የታዩ የሕግ ይዘት እመርታዎች ናቸው:: ያንኑ ያህል ደግሞ፣ ተቋሞችን በመመሥረት፣ አሠራራቸውን በመደንገግና ዘመናዊ በማድረግ ላይ ያተኮሩ ተግባራት ስለነበሩ ከላይ በተገለፁት በሁለቱም የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት የዕድገት እርከኖች ወቅት በሕጎች ይዘትና በተቋማት ግንባታ ረገድ የተከናወኑት ተግባራት የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ተደርገው የሚታዩ ናቸው:: ■

### ሕግጋት

- ፍትሐ ነገሥት
- ለፍርድ ሚኒስትርና ለወንበሮች የተሰጠ ደንብ
- የዳኝነት ሚኒስቴር ደንብ (ባዔ ምኒልክ የተሰጠ፣ ፲፱፻ ዓ/ም)
- ለተበየነበት ሰው ግልባጭ ስለመስጠት ትዕዛዝ (የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን መጋቢት ፳፪ ቀን ፲፱፻፲፩ ዓ/ም)
- ለፍርድ ሚኒስትርና ለወንበሮች የተሰጠ ደንብ (የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን)
- ስለ ነፍሰ ገዳይ የተሰጠ ደንብ (የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን)
- የ፲፱፻፳፫ ዓ/ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ
- ስለዳኝነት ሥራ አካሄድ የወጣ አዋጅ - ቁጥር ፪/፲፱፻፵፩
- ያገር ግዛት ደንብ - ድንጋጌ ቁጥር ፩/፲፱፻፵፩
- ስለ ዓቃብያነ ሕግ የወጣ ያ፲፱፻፵፩ ዓ/ም አዋጅ

[101] ከበደ እንግዳሰው፣ *የምክር ቤታችን ዕድል* (ብርሃንና ሰላም ቀ/ኃ/ሥ ማተሚያ ቤት ፲፱፻፺፫ ዓ/ም) ከገጽ ፺፯ እስከ ፻፩::

- *የ፲፱፻፴፬ ዓ/ም የፖሊስ አዋጅ (ቁጥር ፮)*
- *ስለፍርድ ቤቶች ሥርዓት አፈጻጸም በ፲፱፻፴፭ ዓ/ም የወጣ ደንብ፣የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ. ፴፫/፲፱፻፴፭ ዓ/ም*
- *የ፲፱፻፴፮ ዓ/ም የወህኒ ቤቶች አዋጅ*
- *ያገር አገዛዝ ደንብ ማሻሻያ - ድንጋጌ ቁጥር ፮/፲፱፻፴፫*
- *ስለጠቅላይ የንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥነ-ሥርዓት ፲፱፻፵፫ ዓ/ም የወጣ ደንብ፣ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር ፩፻፺፰/፲፱፻፵፫*
- *ስለዳኝነት ሥራ አካሄድ ማሻሻያ የወጣ ዐዋጅ - ቁጥር ፩፻፪/፲፱፻፵፩*
- *የዓቃብያነ ሕግ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፰/፲፱፻፵፫*
- *የ፲፱፻፶፭ ዓ.ም ስለፍርድ ቤቶች የወጣ አዋጅ - ቁጥር ፻፺፭/፲፱፻፶፭*
- *ስለአጥቢያ ዳኞች አቋቋም የወጣ ዐዋጅ - ቁጥር ፫/፲፱፻፴፱*
- *የኢትዮጵያ ፌደራል የዳኝነት ሥልጣን አዋጅ - ቁጥር ፩፻፴/፲፱፻፵፭*
- *የፌደራል የዳኝነት ሥልጣን ማሻሻያ አዋጅ - ቁጥር ፩፻፴፩/፲፱፻፵፮*
- *ስለፍርድ ቤቶች ሥርዓት አፈጻጸም በ፲፱፻፴፭ ዓ.ም የወጣ ደንብ - የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር ፴፫/፲፱፻፴፭*
- *የ፲፱፻፷፭ ዓ.ም የዳኞች አስተዳደር አዋጅ - ቁጥር ፫፻፫/፲፱፻፷፭*
- *የፌደራል ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፵፮*
- *ስለሕዝባዊ መብት የወጣ አዋጅ ቁጥር ፻፴፱/፲፱፻፵፮*
- *የንጉሠ ነገሥቱን ግዛት ጸጥታ ስለሚነኩ አንዳንድ ወንጀለኞች የዳኝነት ሥራ አካሄድ የወጣ ዐዋጅ - ቁጥር ፹፮/፲፱፻፴፱*
- *ስለዳኝነት ሥራ አካሔድ የወጣ አዋጅ - ቁጥር ፺፪/፲፱፻፷፯*

**ሌሎች ሰነዶች**

*ከሕግ መርማሪ ጉባዔ ለሚንስትሮች ም/ቤት የቀረበ የሕግ ረቂቅ ቁ ፩፻፹፯ (መስከረም ፱ ቀን ፲፱፻፶፬ ዓ/ም)*

---

## ዋቢ ጽሑፎች


ሀብተማርያም ወርቅነህ፣ *የጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት* (አዲስ አበባ፣ 2013 ዓ/ም)

መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ *የሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፤ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት* 1896-1922 (ሦስተኛ እትም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ፪ሺ. ፪ ዓ.ም)

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ *ዝክረ ነገር* (ሁለተኛ እትም ፲፱፻፷፪ ዓ.ም አዲስ አበባ)

ቅጣው ይታጠቁ፣ *ስለዳኝነት* (ብርሃንና ሰላም ማተሚያ1954 ዓ/ም)

ባሕሩ ዘውዴ፣ *ፋና ወጊ የለውጥ አቀንቃኞች በኢትዮጵያ፤ በሃያኛው መቶ ዓመት መባቻ* (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ 2013 ዓ/ም)

አበራ ጀምበሬ፣ *የኢትዮጵያ ሕግና የፍትሕ አፈጻጸም ታሪክ ከ1426 እስከ 1966 ዓ/ም* (ሻማ ቡክስ 2006 ዓ/ም)

አበራ ጀምበሬ «ተጠየቅ ሙግት፥ ልማዳዊው የኢትዮጵያ የክርክር ስልት» *የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት፣* ቅጽ ፲፭ (፲፱፻፹፬ ዓ/ም)

እምሩ ኃይለ ሥላሴ፣ *ካየሁት ከማስታውሰው፣* 2ኛ እትም (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፪ ሺ. ፪ ዓ/ም)

ከበደ እንግዳሰው፣ *የምክር ቤታችን ዕድል* (ብርሃንና ሰላም ቀ/ኃ/ሥ ማተሚያ ቤት ፲፱፻፶፫ ዓ/ም)

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፣* ፩ኛ መጽሐፍ ፪ኛ እትም (ብርሃንና ሰላም ቀ/ኃ/ሥ ማተሚያ ቤት ፲፱፻፷፭ ዓ/ም)

ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም፣ *ኦቶባዮግራፊ (የሕይወቴ ታሪክ)* (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ፪ሺ፫ ዓ/ም)

ጀ ቫንደርሊንደን «የኢትዮጵያ ሕግ ምንጮች መግቢያ፤ ከ፲፫ኛው እስከ ፳ኛው መቶ ዓመት» *የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት* ቅጽ ፫ ቁጥር ፩ (፲፱፻፶፱ ዓ/ም)

ዣን ግራቨን «የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ» የኢትዮጵያ የሕግ *መጽሔት* ቅጽ ፩ ቁጥር ፪ (፲፱፻፶፯ ዓ/ም)

Marein, Nathan (1954). The Ethiopian Empire -Federation and Laws (Royale Netherlands Prining and Litograhing Company).

Gebre-Sillasie (2017). *Chronicles of the Reign of Menilek II King of Kings of Ethiopia,* Vol I (Trans. Dominique Lusser, Tsehai Publisher)